# መልካም እረኝነት

ክርስቲያናዊ መሪነት በ፫ኛው ሺህ ኢትዮጵያ

ቅጽ ፫ በመንፈሳዊ መሪነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች



መልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)

የቅጂ መብት - © መልሳቸው መስፍን - 2005

© Melisachew Mesfin – 2013

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
ይህን መጽሐፍ ለንግድ ወይም ትርፍ ለሚያስገኝ ሥራ በሙሉም ሆነ በከፊል አባዝቶ መጠቀም አይፈቀድም:: ሆኖም በደራሲው ፈቃድ ለማስተማር አገልግሎት በጥቂትም ሆነ በብዙ አባዝቶ በነጻ ማሰራጨትና መጠቀም ይበረታታል፡፡

በክፍሉ ካልተጠቀሰ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1962 ዓ.ም. ከታተመው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው::

የመጀመሪያ እትም 1999 ዓ.ም.
First printing - 2007

ተስፋፍቶ የተዘጋጀ እትም 2005 ዓ.ም.
Expanded Edition 2013

በመጽሐፉ ላይ አስተያየት ቢኖርዎት ለጸሐፊው በፖ. ሳ. ቁጥር 31716፣ አዲስ አበባ ብሎ መላክ ይቻላል::



# አበርክቶ

በተከታታይ ቅጾች የተዘጋጀውን ይህን መጽሐፍ
ለሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን
ሳበረክት
ከእህት አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመሆን
በ፫ኛው ሺህ ኢትዮጵያ
የሚጠበቅባትን ተልእኮ በሙላት እንድትፈጽም በመመኘትና
በመጸለይ ነው::

# ማውጫ

መግቢያ ........................................ 6
ምዕራፍ 1፡ ዮሴፍ ........................................ 7
ምዕራፍ 2፡- ሙሴ ........................................ 33
ምዕራፍ 3፡- ዳዊት ........................................ 62
ምዕራፍ 4፡- ሕዝቅያስና ኢዮስያስ ........................................ 91
4.1 ሕዝቅያስ ........................................ 91
4.2 ኢዮስያስ ........................................ 101
ምዕራፍ 5፡- ነህምያ........................................ 110
ምዕራፍ 6፡- ጴጥሮስ ........................................137
ምዕራፍ 7፡- ጳውሎስ ........................................163
ምዕራፍ 8፡- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ........................................190

# መግቢያ

በቀደሙት ሁለት ቅጾች የመሪነትን ምንነት፣ ባሕርያት፣ ችሎታዎችና ተግባር ተመልከተናል፡፡ ክርስቲያናዊ መሪነት ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖር ግንኙነትና ፈቃዱን በማገልገል ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ስለ ክርስቲናዊ መሪነት ለመማር ዋናው ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለሆነም በሕይወት ልምምዳቸው ይህን ያሳዩ ሰዎችን ምሳሌነት ማጥናት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ ቅጽ የምናደርገውም ይህንኑ ነው፡፡

በብሉይና በአዲስ ኪዳን ከምናገኛቸው እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉት ብዙ መሪዎች በዚህ ቅጽ የቀረቡት ዘጠኝ ብቻ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ምሳሌዎች ስለ ክርስቲያናዊ መሪነት ምንነት በእጅጉ እንማራለን፡፡ በሁሉም በርካታ ተመሳሳይነት መኖሩን እናስተውላለን፡፡ ዋናው ትምህርት መሪነት ማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ ያንን ማገልገል እንደሆነም በአንክሮ እንገነዘባለን፡፡

በዚህ ቅጽ ፫ ከቀረቡት ዘጠኝ መሪዎች አንዱ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ ከሌሎች መሪዎች ጋር በተርታ የተዘረዘረና ለሌሎች እንደተደረገው ሁሉ ስለ አመራሩ ትንተና የተደረገ ቢሆንም ስለ እርሱ በሙላት ለመግለጽ የሚበቃ ሰው እንደማይኖር ይታወቃል፡፡ የእርሱ ምሳሌነት ፍጹም ነው፡፡ እንደ እርሱ ያለ መሪ አልነበረም፣ አይኖርምም፡፡ ከምሳሌው እጅግ ብዙ እንማራለን፡፡ በመንፈሳዊ እድገት ሁላችንም የምናድገው ወደ እርሱ ሙላት ልክ እንደሆነ ሁሉ በመሪነትም የምናድገው ወደ እርሱ አመራር ደረጃ ነው፡፡

በዚህ ቅጽ የቀረበውን ካጠናን በኋላ ከቅጽ ፩ እስከ ቅጽ ፫ የተማርነውን በማዋሃድና በማጥለል በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለሚገኝ ክርስቲያን መሪ የሚሆን ዋና ትምህርት በቅጽ ፬ እንመለከታለን፡፡ አሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈሳዊ መሪነት ምሳሌዎች አድርገን ከምንመለከታቸው በዮሴፍ እንጀምር፡፡





ምዕራፍ 1

# ዮሴፍ

ዮሴፍ በ1700 ዓ.ዓ አካባቢ በከነዓን የተወለደ የያዕቆብ አሥራ አንደኛ ልጅ ነው (ዘፍ 20:22-24)፡፡ እናቱ ራሔል በአሥራ ሁለት ዓመቱ ወንድሙን ብንያምን ስትወልድ ሞተችበት (35:16-20፤ 48:7)፡፡ ዮሴፍ አባቱ ያዕቆብ የሚወደው፣ ባለ ኅብር ልብስም ያለበሰው፣ የአባቱን በጎች ይጠብቅ የነበረ ወጣት ነበር፡፡

ዮሴፍ በአሥራ ሰባት ዓመት እድሜው እግዚአብሔር ሁለት ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው ሕልሞች እንዳሳየው በዘፍ 37:5-11 እናነባለን፡፡ ሕልሞቹን ለወንድሞቹ በነገራቸው ጊዜ ከእነርሱ ይልቅ ከፍ እንደሚል ከሕልሙ ስለተረዱ ዮሴፍን ጠሉት፡፡ ሕልሙ የሚፈጸምበት ጊዜ መቼ እንደሚሆን ባይታወቅም የሕልሙ ፍቺ ግን በአባቱና በወንድሞቹም ዘንድ የታወቀ ነበር፤ «አባቱም ነገሩን ይጠብቀው ነበር» (37:11)፡፡

ዮሴፍ ለአባቱ ታዛዥ ልጅ ነበር፡፡ በግ ይጠብቁ የነበሩ ወንድሞቹን እንዲጠይቅ በአባቱ የተላከው ዮሴፍ ወንድሞቹን እስከሚያገኛቸው ድረስ ፍለጋውን ቀጠለ፡፡ ይህም ለአባቱ ለመታዘዝ የነበረውን ፍላጎትና ለጠሉት ወንድሞቹም መልእክቱን ለማድረስ ያለውን ቅንነት ያሳያል፡፡ ወንድሞቹ ግን ወደ እነርሱ በቀረበ ጊዜ ተማከሩበት፤ በጉድጓድም ጥለውት እነርሱ ግን ሊበሉ ተቀመጡ፡፡

ጥላቻ በተጠይው ሰው ውስጥ ያለውን ምንም በጎ ነገር እንዳያይ አድርጎ የጠይውን ሰው ዓይን ይጋርዳል፡፡ ወንድሙን የሚጠላ ሰው ርኅራኄ አይኖረውም፡፡ ለእንዲህ ዓይነት ሰው ደስታውና ሳቁ

የሚጠላው ሰው ሲሰቃይ ማየት ይሆናል፡፡ ጥላቻ በጎ ኅሊና እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጉድጓድ አውጥተው ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች በሃያ ብር ሸጡት፡፡ ሲሸጡት ዮሴፍን ለሁልጊዜው እንዳያዩት አድርገው መሸኘታቸው ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊታቸው የዮሴፍ ሕልም እንዳይፈጸም የሚቻላቸውን ያህል መጠበባቸው ነበር፡፡ በውኑ ሰው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይፈጸም ሊከለክል ወይም ዘብ ሊቆም ይችላልን? ከቶ አይችልም፡፡

ወንድሞቹ በፍየል ደም የነከሩትን የዮሴፍን ቀሚስ ወሰዱ፡፡ ያዕቆብ ገና ልብሱን ሲያይ «...የልጄ ቀሚስ ነው፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፤ ዮሴፍ በእርግጥ ተበጫጭቋል አለ። ...ያዕቆብም ልብሱን ቀደደ፥ በወገቡም ማቅ ታጥቆ ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ» (37፡33-34)፡፡ ዮሴፍ ግን በግብጽ በሕይወት ይኖር ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን የሚፈጽምበት ሰው ዮሴፍ መሆኑን ገና ማንም አልተረዳም፡፡

ዮሴፍን የገዙት ነጋዴዎች ወደ ግብጽ ምድር ወስደው የፈርዖን ጃንደረባ ለዘበኞቹ አለቃ ለነበረው ጲጥፋራ ሸጡት (37፡36)፡፡ ዮሴፍ በእግር ብረት ታስሮም እንደ ነበረ ከመዝ 105፡7-19 እንነዘባለን፡፡ ያም ሁሉ ሆኖ ዮሴፍ በግብጽ ምድር ትልቅ ሥልጣን ለነበረው ለጲጥፋራ መሸጡ አጋጣሚ አልነበረም፡፡ ይህም እንኳን እግዚአብሔር በሕይወቱ የሚሠራውን ሥራ የሚያከናውንበት መንገዱ ነበር (ዘፍ 45፡5)፡፡ በጲጥፋራ ቤት ዮሴፍ ለቀሪው ዘመኑ የሚሆን ሥርዓትና ልምድ የሚማርበት ቦታ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በዚያ ቤት እግዚአብሔር ሞገስን ሰጥቶታል፡፡





በዚያ ቤት የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን የፈተነችበትና በእርግጥ እርሱ ደግሞ እግዚአብሔርን እንደሚፈራ የታየበት ቦታም ነበር፡፡ ይህች ሴት ዮሴፍን ስትፈትነው በሰው ደረጃ ጉዳዩ በምሥጢር ተጠብቆ እንደሚቀር አድርጋ አመቻችታ ነበር፡፡ ምናልባትም በሁለቱ መካከል ብቻ ተደብቆ የሚቀር ጉዳይ ሊሆን በቻለም ነበር፡፡ ሆኖም ዮሴፍ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስለ ነበረ ሁልጊዜ ኑሮው በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ እንደሆነ ያውቃል፡፡

ዮሴፍ በሕልሙ ያየው የእርሱ ነዶ ቀና ሲል ቢሆንም የሚፈጸምበት ጊዜ ገና ነበርና እስኪፈጸም ድረስ ራሱ አጎንብሶ ተጓዘ፡፡ ወደ ጉድጓድና ወደ ወኅኒ ተጣለ፡፡ እግዚአብሔር በአንድ ሰው ሕይወት የጀመረውን ዓላማ በራሱ ጊዜና ጥበብ በመሥራት ዳር የሚያደርስ አምላክ ነው፡፡

ዮሴፍን ወንድሞቹ ቢጠሉትና ለባርነት ቢሸጡትም በከነዓን ሕልም ያሳየው እግዚአብሔር በሚሄድበት ሁሉ (በግብጽም) አብሮት ከእርሱ ጋር ነበር፡፡ ዮሴፍን ተከትሎ የሚሄድና መዳረሻውን የሚያይ ማንም ባልነበረበት ሁኔታም ቢሆን እግዚአብሔር ግን የእርሱ መድረሻው ነበር፡፡ ዮሴፍ ባሕሉንና ቋንቋውን ወደማያውቀው ሕዝብ ተወስዶ ቢሸጥም እግዚአብሔር ግን በዮሴፍ ላይ የሚሆነውን ሁሉ ይቆጣጠር ነበር፡፡ የሰው ባሪያና እስረኛ፤ ባለ ሕልምና የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር፡፡

ወጣቱ ዮሴፍ ኃጢአት ማድረግ እግዚአብሔርን መበደል እንደሆነ ያስተዋለ ሰው ነበር፡፡ ከዚያ ፈተና ለመውጣት ልብሱን ጥሎ መሸሽ ለዮሴፍ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍለዋል፡፡ በጊዜው ስሙ ይጎድፋል፡፡ ወደ እስር ቤት መጣልንና ቅጣትን ያስከትላል፡፡ ነገር ግን ጻድቅ ሰው ጊዜያዊ ለሆነ የስም መጉደፍና መዋረድ አያዝንም፡፡ ጻድቅ ሰው ሁልጊዜም ቢሆን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ይጥራል፤ በፊቱ ያለውን ሽልማት ይቀበል ዘንድ ነውርን ይንቃል፡፡

ዮሴፍ ወደ እስር ቤት ከተጣለ በኋላ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ (39:21-23):: ይህን ወጣት እግዚአብሔር አልተወውም:: ምሕረትን አበዛለት:: እናስተውል፡- ዮሴፍ ወደ ጉድጓድና ወደ እስር ቤት እንዳይጣል ለማድረግ እግዚአብሔር ይቻለዋል:: ነገር ግን ከዮሴፍ ጋር የነበረ እግዚአብሔር በጉድጓድና በእስር ቤት መጣሉን ለትምህርቱና ለሥልጠናው አደረገለት:: ብቻ እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጋር ይሁን እንጂ ያ ሰው እንደ ዮሴፍ በጉድጓድ ቢጣል፤ ቢሸጥ፤ እስር ቤት ቢገባ ይህ ለእግዚአብሔር የማስተማሪያው መንገድ ይሆናል::

ከእርሱ ጋር የነበረው እግዚአብሔር ለዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ ሞገስን ሰጠው:: ዮሴፍ ለሌሎች እስረኞች ያስብ የነበረ (ግድ የነበረው) ሰው ነበር:: ዮሴፍ ራሱ በእስር ላይ የነበረ ሰው ቢሆንም ሌሎች እስረኞችን ያጽናና ነበር (ዘፍ 40:7-8):: ይህ በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው ባሕርይ ነው:: ዮሴፍ በሕልም ምክንያት በወንድሞቹ የተጠላ፤ ወደ ጉድጓድ የተጣለ፤ የተሸጠ፤ ሰው ነው:: ለደረሰበት መከራ መነሻው በሕልሙ ምክንያት ወንድሞቹ ስለ ጠሉት እንደሆነ ዮሴፍ ያውቃል:: ስለሆነም ገና ያልተፈታ ሕልም የነበረው ሰው ነው:: ዮሴፍ - ሕልሙ ያልተፈታለት ሕልም ፈቺ!!

ዮሴፍ ከነበረበት እስር ቤት በድንገት ተጠርቶ ለፈርዖን ሕልሙን ከፈታለት በኋላ የሕልሙን ፍቺ በተግባር እንዲያውል ፈርዖን ዮሴፍን ሾመው:: ከዚህ ጊዜ በኋላ ዮሴፍ ያየው የረጅም ዘመን ሕልም እውን መሆን ጀመረ:: ዮሴፍ ሕልምን ባየበትና በተሾመበት ጊዜ መካከል 22 ዓመታት ያህል የጊዜ ርዝመት አለ::[1] ዮሴፍ

[1] ዮሴፍ ሕልም ሲያልም የ17 ዓመት ልጅ ነበር (ዘፍ 37:2:5):: ከ13 ዓመታት በኋላ በተሸጠበት አገር በፈርዖን ፊት ሲቀርብና ሲሾም የ30 ዓመት ሰው ነበር (41:46):: ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ 7 የጥጋብ ዓመታት ነበሩ (41:26 29 47):: የራብ ዘመን ከጀመረ ከ2 ዓመት ያህል በኋላ ደግሞ ወንድሞቹ ስንዴ ሊገዙ ወደ ዮሴፍ መጡ (42:6፣ 45:6):: ስለዚህ የዮሴፍ ሕልም መፈጸም የጀመረው ሕልሙን ካየ ከ22 ዓመት (13+7+2) በኋላ ነበር::





ሕልሙን ያየው በራሱ ሀገር በከነዓን ከአባቱ ጋር እያለ ነበር:: ሕልሙ መፈጸም የሚጀምረው ከብዙ ዓመታት በኋላ፤ በባዕድ ምድር፤ ማንም የእርሱ ወገን የሆነ ሰው በሌለበት ቦታ ነው::
ዮሴፍ እግዚአብሔር አምላኩን የሚከተለውና የሚያስበው በሁሉም አገር፤ ቦታና ጊዜ እንደ ነበረ ከልጆቹ ስም አወጣጥ ሳይቀር ማየት እንችላለን:: «እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአባቴንም ቤት አስረሳኝ» ሲል የመጀመሪያውን ምናሴ፤ «እግዚአብሔር በመከራዬ አገር አፈራኝ» ሲል ደግሞ ሁለተኛውን ኤፍሬም ብሎ ጠራቸው (40:52):: ዮሴፍ የመከራ ሰው ነበር:: መከራን መርሳት በእግዚአብሔር እንደሆነም አውቋል:: ላገኘው በረከት እግዚአብሔርን ያመሰግናል::

እግዚአብሔር በእርሱ ለሚያምኑት ብቻ ሳይሆን ለማያምኑትም እንኳን የሚናገርበት መንገድ አለው:: በግብጽ ምድር ራብ እንደሚመጣ ለፈርዖን በሕልም ገለጠለት:: ዮሴፍ የሕልሙን ፍቺ ከተረዳ በኋላ ምን መደረግ እንዳለበትም ለፈርዖን ይነግረዋል (41:46-49):: ሕልሙ ደጋግሞ መታየቱም ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ መሆኑን ያስረግጥለታል (41:32):: የዮሴፍ ዋናው ምክር ለሚመጣው ሰባት የራብ ዘመን አስቀድሞ በቂ ዝግጅት ይደረግ የሚል ነበር:: እግዚአብሔር ሀሳቡን ለሰዎች በሕልም፤ በራእይ ወይም በልዩ ልዩ መንገድ የሚናገረው ወደፊት ሊሆን ያለውን ለማስታወቅ ብቻ ሳይሆን ሰዎች ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር በመተባበር የድርሻቸውን እንዲያደርጉ ለመምከርና ለመልካም እንዲሆንላቸው ጭምር ነው::

ዮሴፍ ሕልም ካየ በኋላ የነበሩት 13 ዓመታት ካየው ሕልም በተቃራኒ የሄደባቸው ጊዜያት ነበሩ:: እርሱ እንደ ሕልሙ ከፍ ብሎ ከመታየት ይልቅ ዝቅ ዝቅ የተደረገበት፤ ልብሱን የተገፈፈበት፤ የተሸጠበት፤ ወደ እሥር ቤትም የተጣለበት ጊዜ ነው:: በእነዚህ ዓመታት የደረሰበት ችግርና ፈተና ያየውን ሕልም እስከሚረሳው

ድረስ ሊያደርሰው እንደሚችል መገመት ይቻላል:: ለመሆኑ የተስፋ መፈጸም በስንት ዘመን ውስጥ ይመጣል?

እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ለማድረግ ሙሉ ሥልጣን አለው:: ተስፋ ይሰጥ ዘንድ የሚያስገድደው ማንም እንደሌለ ሁሉ የሰጠውን ተስፋ ይፈጽመውም ዘንድ ማንም አያግዘውም:: እግዚአብሔር በነፃ ፈቃዱ ተስፋን ይሰጣል፤ በፍጹም ሥልጣኑ ተስፋን ይፈጽማል:: ይህንም የሚያደርገው በራሱ የጊዜ ተመን ነው:: ለአብርሃም ልጅን እንደሚሰጠው የገባውን ተስፋ የፈጸመው ከ25 ዓመታት ያህል በኋላ ነበር:: ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደሚመለሱ ለእስራኤላውያን ተስፋ የሰጣቸው ዘመን ተምኖ «ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ» (ዘፍ 15:16፤ ዘጸ 12:41) በማለት ነበር:: የዮሴፍም የሕልሙ ፍቺ መከናወን የጀመረው ሕልሙን ካየ ከ22 ዓመታት ያህል በኋላ ነበር::

በዮሴፍ ሕይወት እንደሆነው የሰጠውን ተስፋ እውን ለማድረግ እግዚአብሔር የሚነሣባት አንዲት ሌሊት በቂ ነች:: መርዶክዮስ ከተቀመጠበት ተነሥቶ በክብር ከተማዋን እንዲዞርና እንዲሾም ያስደረገች ከንጉሡ እንቅልፍ የተከለከለባትና መጽሐፍ የተገለጠባት አንዲት ሌሊት ናት:: ዮሴፍ ከእስር ቤት ወደ መንግሥት የመጣው በአንዲት ሌሊት ነበር:: እስራኤላውያን ከግብጻውያን መከራ ያረፉበት፤ ዳግመኛም እንዳያዩአቸው የሆኑበት በአንዲት ሌሊት ነበር (ዘጸ 14:9-10፤ 19-20):: እግዚአብሔር ከረጅም ጊዜ በፊት የገባውን ተስፋ ለመፈጸም ሊያደርገው በወደደ ጊዜ ያን ጊዜ ከመቅጽበት ይሆናል::

በግብጽ ምድር ወደ ሹመት ከመጣ በኋላ ዮሴፍ ከፈርዖን ቀጥሎ ሥልጣን ያለው ሰው ሆነ:: የእግዚአብሔር አሠራር በሰው ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚገለጥ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ትናንት ባሪያ እንዲሁም እስረኛ የነበረን ሰው ዛሬ ለክብር፤





ለሹመት፤ ለሥልጣን ሊያበቃው እርሱ እግዚአብሔር ይቻለዋል:: እግዚአብሔርን እንዴት ታደርጋለህ? ብሎ የሚጠይቀው ማነው? የእግዚአብሔር ሀሳብ አይከለከልም::

ዮሴፍ በሥልጣን እጅግ ከፍ ባለ ቦታ ሆኖ እያለ ስንዴ ለመግዛት ወደ ግብጽ የመጡ ወንድሞቹን ሲያያቸው ራሱን ከወንድሞቹ ጋር ለማመሳሰልና እነርሱ የእርሱ ወንድሞች መሆናቸውን በፈርዖን ፊት ለመግለጽ አላፈረም (ዘፍ 47:1):: ስለተቸገሩ እህል ለመግዛት የመጡ «የሌላ አገር ዜጎች» በሆኑ ወንድሞቹ ላይ አላፈረም፤ ራሱንም አልደበቀም:: የጠሉት፤ የሸጡት፤ በእረኝነት ተግባር የሚኖሩ፤ በግብጻውያን ፊት የተናቁ ሰዎች ቢሆኑም (ዘፍ 43:32) በፈርዖን ፊት ወንድሞቼ ብሎ ይጠራቸዋል:: ማንነቱን የማይሸፍን እውነተኛ ሰው ነው::

ዮሴፍ አባቱ ያዕቆብ በስተእርጅናው ወደ ግብጽ መጥቶ እንዲኖር አደረገ:: ያዕቆብም የዮሴፍን ልጆች በእምነት ባረካቸው (ዕብ 11:21):: የራሱን ልጆች ሲባርክ እንዲሁ የዮሴፍን ልጆችም ባረከ:: የወደፊቱን በሚያውቅና በሚቆጣጠር በእግዚአብሔር የታመነው ያዕቆብ ልጆቹን በመባረክ ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ (ዘፍ 48:8-20)::

ዮሴፍ እግዚአብሔርን የሚያምን የእምነት ሰው ነበር:: እግዚአብሔር ለአብርሃም የተናገረውን ተስፋ እርሱም በዘመኑ ተቀብሎ በእምነት የኖረ ሰው ነበር:: እስራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡ እግዚአብሔር ወደሚሰጣቸው ምድር አጥንቱን ወስደው እንዲቀብሩት በእምነት ተናገረ (ዘፍ 50:25):: ዮሴፍ መቶ አሥር ዓመት ዕድሜ ኖረ::

ከዮሴፍ የሕይወት ጉዞ በመነሣት ስለ መንፈሳዊ መሪነት የምንማረውን ከማየታችን በፊት እዚህ ላይ ጥያቄዎች ማንሣት መልካም ይሆናል:: ለመሆኑ:-

- እግዚአብሔር የሚሾመው ሰው ተስፋውን ለመቀበል ለስንት ዓመት መጠበቅ አለበት?
- አንድ የተሰጠ ተስፋ የሚፈጸመው በየት አገር ነው? በምን ሁኔታ ይሆን?
- አንድ ሰው መሪ ለመሆን በመከራ ውስጥ ማለፍ ያስፈልገዋል ወይ?
- የተሰጠ ተስፋ እንዳይፈጸም የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግ የሚከላከሉ የቅርብ ሰዎች ወይም ወንድሞች ሊሆኑ ይችላሉን?

ለእነዚህና ተመሳሳይ ለሆኑ ጥያቄዎች የምንሰጠው ትክክለኛ መልስ የሚመሠረተው ስለ እግዚአብሔር ታላቅነትና ሁሉን አዋቂነት በሚኖረን ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ ነው:: የተስፋ መፈጸምን የሚጠባበቅ ሰው ሁልጊዜ ሊያስተውል የሚገባው ነገር የእግዚአብሔር አሠራር ከእርሱ ሀሳብ በላይ መሆኑን ነው:: ስለሆነም እግዚአብሔር በሚመራው መንገድ እርሱን ተስፋ አድርጎና ከሀሳቡ ጋር ተስማምቶ እርሱን «የሙጥኝ» ብሎ መጓዝ አለበት::

እንግዲህ ከዮሴፍ የሕይወት ጉዞና ልምድ በመነሣት ስለ መንፈሳዊ መሪነት ቢያንስ የሚከተሉትን አንኳር ነገሮችን መገንዘብ እንችላለን::





### 1. መሪ እግዚአብሔር እንዲሆን በፈቀደው[2] ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የሚያልፍ ነው::

ዮሴፍ በአባቱ የተወደደ ልጅ ነበረ፤ ግን በጉድጓድ ተጣለ (ዘፍ 37:24፤ 42:21)፤ ነፍሱም ተጨነቀ፤ ተሸጠ (37:28):: የሰው አገልጋይ (39:4)፤ ባሪያ ሆነ (39:17):: በጲጥፋራም ሚስት ተፈተነ (39:12)፤ በእስር ቤት ተጣለ (39:20):: ለዚህ ሁሉ የሚያበቃው ምንም አላደረገም (40:15):: ዮሴፍ ሌላ ቋንቋ በሚናገር ሕዝብ መካከል ኖረ (42:13)፤ ከሌላ ወገን ስለሆነ ከሕዝቡ ጋር አብሮ አይበላም (43:32) ነበር:: የተናቀ ሰው ነበር::

ዮሴፍ ሕልም ያለመው ወድዶ (ፈልጎ) ነውን? ሕልምን ለዮሴፍ ያሳየው እግዚአብሔር ነው:: ከያዕቆብ ልጆች ከዮሴፍ ሌላ ሕልም ያለመ ማን ነው? በባለ ሕልሙ የሚቀኑት ወንድሞቹ ቢቻላቸውስ ኖሮ ለየራሳቸው ምነው ጥሩ ሕልም ባለሙ!

ዮሴፍ ሕልም ካለመ በኋላ በሕይወቱ የደረሰው ሁሉ እንደሚጠበቀው አልነበረም:: በወንድሞቹ መጠላቱ፤ በጉድጓድ መጣሉ፤ መሸጡ፤ ባሪያ መሆኑ፤ ወደ እስር መውደቁ ወዘተ. ሁሉ ዮሴፍ ከሚጠብቀው ተቃራኒ እንደሆነ ግልጽ ነው::

ዮሴፍ ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነበረው:: ቃሉ የሚፈጸመው ግን መቼ ነው? «ቃሉ እስኪመጣለት ድረስ የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው»[3] (መዝ 105:19):: ቃሉ እስኪፈጸም ድረስ የደረሰበት መከራ ሁሉ ለዮሴፍ ለሌላ ኃላፊነት የዝግጅት ጊዜ ነበር:: በእነዚህ ዓመታት ዮሴፍ የገባው በእግዚአብሔር የማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ነበር::

[2] Permissive will vs decretive will of God.

[3] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፦ «የተናገረው ቃል እስኪፈጸምለት፣ የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው»:: *

እግዚአብሔር አስተማሪ ነው (ኢዮ 36:22)። እንደ እርሱም ያለ አስተማሪ የለም። የማስተማሪያውንስ መንገድ ማን ያውቀዋል? እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ትምህርት ቤት አለው። እያንዳንዱንም ሰው ያስተምረዋል፤ ያሰለጥነዋል። የእግዚአብሔር የማስተማሪያው መንገድ አንድ-ለአንድ ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው በአቅሙና ለወደፊት ለሚኖረው አገልግሎት በሚስማማ ሁኔታ የሚቀርጸው የትምህርት ዝርዝር (ካሪክለም) አለው። ዮሴፍ በወንድሞቹ ከተጠላበት ጊዜ አንስቶ በሌላ ምድር እስከተሾመበት ጊዜ ድረስ የተማረው የትምህርት ዓይነት ሌሎች እነ ሙሴ፤ ዳዊት፤ ነህምያ፤ ወዘተ. ከወሰዱት ትምህርት በዓላማው (ግቡ) አንድ ቢሆንም በይዘቱ የተለየ ነበር።

«ዘመናዊ» የማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ባልነበረበት ዘመን እግዚአብሔር ዮሴፍን ያስተምረው፤ ያዘጋጀው፤ ያለማምደው ነበር። ከፍ ወዳለ የሥልጣን ኃላፊነት የተመረጠው በእስር ቤት እያለ ነበር።

እግዚአብሔር ዮሴፍን ለኃላፊነትና ለመሪነት ያሰለጠነበትን መንገድ ስናስብ ስለ ልብስ አሠራር ምሳሌ ልንወስድ እንችላለን። በሀገራችን የሽማ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ጥጡን ከመልቀም አንስቶ ጨርቅ (ልብስ) ሆኖ እስከሚወጣ ድረስ የሚከተሉት የአሠራር መንገድ የሚያስደንቅ ነው። ጥጡ ከእርሻ ከተለቀመ በኋላ ቆሻሻ ካለበት ቆሻሻው ይነሳል፤ ፍሬውና ጥጡ ይለያያል፤ ከዚያም ይዳመጣል፤ ይቦጨቃል፤ በደጋን ይባዘታል፤ በጥጡ ውስጥ ቆሻሻ እስከማይኖርና እስኪፍታታ ድረስ በደንብ ይባዘታል። የተባዘተው እየከረረ ክር እስኪወጣው ድረስ በባለሙያ እጅ ይፈተላል። ለሸማ ዕቃ በሚስማማ መንገድ በአንድ በኩል ልቃቂት ሲዘጋጅ በሌላ በኩል ደግሞ ድሩ ከተደራ በኋላ በሙቅ (በአፍላል) ውስጥ ይቀቀላል።





አቤት! ጥጡ የሚናገር ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ለምን ታደርጉብኛላችሁ? ብሎ በጮኸ ነበር።

ጥጡን መልቀም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በቅደም ተከተል የሚያደርገውን ሁሉ ለምን እንደሚያደርገው ሸማ ሠሪው ያውቃል። መጨረሻ ላይ የሚለበሰውን ልብስ በርቀት አይቷልና። ስለሆነም ለጥጡ የሚመልስለት እኔ የምሠራውን አውቃለሁ፤ ጥጥ ሆይ! ከሥራዬ ጋር ብትስማማ በመጨረሻ የተጣልክ ሳይሆን በሰው ላይ የምታርፍ፤ የምትወደድ ልብስ ትሆናለህ በማለት ነው። እንግዲህ ድሩ በሙቅ ውስጥ ካለፈ በኋላ በሸማ ዕቃ ላይ ገብቶ በሸማ ሠሪው ጡንቻ እየተስተካከለና እየተመታ ይሠራል። ሸማ ሠሪውም በአውቀቱ እንደሚፈልገው ዓይነት ጥበብ አድርጎ ይሠራዋል። ጥጡ ይህን ሁሉ «ታግሦ» ያማረ ሸማ ሆኖ ሲወጣ ጥሩ ዋጋ የሚያወጣ፤ የሚወደድና የከበረ ልብስ ይሆናል።

ለዮሴፍ አንዱ የመሰልጠኛው መንገድ በመከራ ማለፉ ሲሆን ሌላው ደግሞ የኃላፊነት ልምምዱ ነው። ዮሴፍ የእግዚአብሔር ቃል እስኪመጣለት ድረስ በቆየባቸው ሁኔታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ኃላፊነት ቦታ እያወጣ ያለማምደው ነበር። ባሪያ ሆኖ በተሸጠበት በግብጽ ምድር በጲጥፋራ ቤት ተሹሞ ነበር (39:4-5)። እንዲሁም ወደ ግዞት በተጣለበት ቦታ ተሹሞ ነበር (39:22-23)። በኋላም በግብጽ ምድር ላይ ተሾመ (41:40-41)። ይህም የመሰልጠኛ ሌላው መንገድ ነበር።

እንዲሁ በእግዚአብሔር መሰልጠን የሚፈልግ ሰው ባለበት በማንኛውም ሁኔታ የተሰጠውን ኃላፊነት ሳይንቅ ሁልጊዜ በአግባቡ ለመሰልጠን የተዘጋጀ ሰው ነው። እግዚአብሔር መሪዎችን የሚያሰለጥንበት መንገድ አንዳንድ ጊዜ መከራ የበዛበት ቢመስልም ዓላማው ሠልጣኙ የሚያምርና የሚፈለግ «ጥበብ»፤ «ትሑት አገልጋይ» ሆኖ እንዲሠራ ነው። መሪዎች እግዚአብሔር

ወደሚፈልገው ቦታ እስከሚያደርሳቸው ድረስ በሚያሳልፋቸው መንገዶች ከእርሱ እየተማሩ ቢሄዱ ያ እውነተኛ ትምህርት ቤት ነው:: እግዚአብሔር በዚህ ትዕግሥትን፤ ትሕትናን ያስተምራል::

## 2. መሪ በማንኛውም ሁኔታ እግዚአብሔርን ይፈራል፤ ከኃጢአትም ይሸሻል::

ዮሴፍ ከዘመዶቹ ተለይቶ ወደ ሌላ አገርና ባሕል ሲገባ በዚያ በወጣትነት «አፍላ» ዕድሜው ባሕርይውን አልቀየረም:: «በማልታወቅበት ምድር ስለ ገባሁ» በሚል ቀድሞ ይከተለው ከነበረው ከአምላኩ ከእግዚአብሔር አልራቀም፤ ከሚያውቀውም እምነት በተለየ ሁኔታ አኗኗሩን አልለወጠም:: ኑሮው በባዕድ አገርና እርሱን በማያውቀው ሕዝብ መካከል ቢሆንም በሁሉም ቦታና ሁልጊዜ እርሱን የሚያውቀው «አንዱ እግዚአብሔር» እንዳለ ያውቃል::

ዮሴፍ ኃጢአትን መሥራት ማለት እግዚአብሔርን መበደል እንደሆነ ያውቃል:: የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን የፈተነችው በራሷ መንገድ ተጠብባ ሁሉ ነገር በድብቅ እንዲቀር ያዘጋጀችው ከፉ ወጥመድ ነበር:: ዮሴፍ ግን «...እነሆ ጌታዬ በቤቱ ያለውን ምንም ምን የሚያውቀው የለም፥ ያለውንም ሁሉ ለእኔ አስረከበኝ፤ ...እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (39:8-9) በማለት ታማኝነቱ ለምድራዊ አለቃውና ለሰማያዊ አምላኩ እንደሆነ ገለጸ::

ዮሴፍ «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ» ሲል የእግዚአብሔርን ሕያውነት፤ ቅድስናና በሁሉም ቦታ መገኘት የተገነዘበ ሰው መሆኑ ግልጽ ነው:: በከነዓን ያመልከው የነበረው





እግዚአብሔር በግብጽም አብሮት እንዳለ ያውቃልና:: ስለዚህ ከተዘጋጀለት ወጥመድ ሸሸ::

ሰው የዝሙትን ኃጢአት የሚፈጽመው በሥጋው ቢሆንም ኃጢአትነቱ ግን በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠና እርሱንም የሚያሳዝን ነው:: እንዲህ ዓይነቱን ኃጢአት ላለመሥራት ዋነኛው መንገድ መሸሽ ነው (2ጢሞ 2:22):: ዮሴፍ ኃጢአትን በመሥራት እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ይልቅ ባለመሥራቱ ምክንያት የሚመጣበት መከራ ካለ ያንን መቀበልን መርጧል:: ኃጢአትን ሠርቶ ከሌላ ሰው መደበቅ ይቻል ይሆናል፤ ከእግዚአብሔር ፊት ግን መደበቅ አይቻልም:: ስለሆነም መንፈሳዊ መሪ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እንደሚታይ በማወቅ መመላለስ፤ በእርሱም ጸጋ በመደገፍ ከኃጢአት መሸሽ ይገባዋል::

ከኃጢአት መሸሽ (ወይም ራስን በንጽህና መምራት) በውጭ ባሉት ዘንድ የሚያስመሰግን ነገር ላይሆን ይችላል:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ መናቅና ስድብን ያስከትል ይሆናል:: ክርስቲያን መሪዎችም ትክክለኛ ነገር በመፈጸማቸው ወይም ከኃጢአት ጋር ባለመተባበራቸው ከማያምኑት ዘንድ መልካም ስም (ብድራት) መጠበቅ የለባቸውም:: መልካም ስም ቢመጣ ጥሩ፤ ሆኖም በመልካም ፈንታ ክፉ ሊመጣ እንደሚችል ከዮሴፍ ሕይወት እናስተውላለን:: መሪዎች ዋጋን የሚጠብቁት ከሰዎች ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን መዘንጋት አይኖርባቸውም::

እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው በችግሩ ጊዜ (በዝቅተኛ ኑሮ እያለ) ይፈራዋል፤ ሥልጣንም ሲይዝ ይፈራዋል:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በየትኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ ቢገኝ ባሕርዩ ተመሳሳይ ነው::

## 3. የመሪ ሞገሱ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑ ነው::

ዮሴፍ እግዚአብሔርን በመፍራቱ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ:: እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያለ ሰው ሞገስን ያገኛል፤ ጥበብ ይበዛለታል፤ በመከራም ውስጥ ቢያልፍ እግዚአብሔር ከመከራው ያወጣዋል::

«እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ» (39:2-3፤ 21፤ 23፤ ሐዋ 7:9) እና ዮሴፍ በፈርዖን ፊት «ቢትወደድ»[4] (7፤10) ሆኖ እንዲሾም ሞገስና ጥበብን ሰጠው:: እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበርና በጲጥፋራ ቤት መከናወንን ሰጠው:: የተሰጠውን ኃላፊነት በጥንቃቄ ተወጣ ያልተሰጠውን ደግሞ ላለማድረግ ራሱን ገዛ:: ይህም ታማኝነት[5] ነው::

እግዚአብሔር ሕልምን ካሳየው ሰው ጋር አብሮ ይሆናል:: እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደ ነበረ ሁሉ እርሱን ከሚፈራውና ፈቃዱ በሕይወቱ እንዲፈጸም ከሚስማማ ሰው ጋር አብሮ ይሆናል:: የሚያከብሩትን የሚያከብር እግዚአብሔር (1ሳሙ 2:30) ለዮሴፍ የሥራ መከናወንን ሰጠው (39:2፤3፤23):: ምሕረትና ሞገስም በዛለት (39:21-24):: ከዮሴፍም የተነሣ ሌሎች በረከትን አገኙ (39:5)::

እንግዲህ አንድ መሪ በእርምጃው ሁሉ ሊጠይቀው የሚገባው <u>ትልቅ ጥያቄ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር አለ ወይ</u>? በማለት ነው:: ምክንያቱም «እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም ነበር» (መሳ 16:20) ተብሎ እንደተጻፈለት እንደ ሶምሶን ሆኖ መገኘትም ስላለ ነው:: እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ ያወቀ ሰው ደግሞ በአገርም ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ፤ ለብቻውም ሆነ ከዘመዶቹ ጋር፤

---

[4] "Governor" KJV, "ruler" ESV.

[5] integrity





በደስታ ጊዜም ሆነ በችግር ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚያየው ያውቃል፤ ይፈራዋል::

## 4. መሪ እግዚአብሔር የሁሉ ጌታና የታሪክ ባለቤት እንደሆነ የሚገነዘብ ነው::

ዘማሪው ስለ ዮሴፍ ሲናገር «የቤቱ ጌታ የጥሪቱ ሁሉ ገዢ አደረገው፤ አለቆቹን እንደ ፈቃዱ ይገሥጽ ዘንድ ሽማግሌዎቹንም ጥበበኞች ያደርጋቸው ዘንድ» (መዝ 105:21-22) ይላል:: ዮሴፍ በሌላ ምድርና «በሌሎች» ላይ ጌታና ገዢ ሆኗል:: በሌላ ምድርና በሌሎች ላይ አለቃ፤ አስተማሪ፤ ሌሎችን የሚገስጽና የሚመራም ነበር::

ዮሴፍ ሕልምን ባለመ ጊዜ ሕልሙ የሚፈጸመው በወንድሞቹ መካከል እንደሚሆን መገመት ከባድ አይደለም:: ወንድሞቹን አስመልክቶ ያየው የሕልም ፍቺም በጊዜው ተከናውኖአል:: እግዚአብሔር በዮሴፍ ሕይወት የፈጸመው ግን በቅርብ ካለው (ከቀጥተኛው) የሕልም ፍቺ ባሻገርና የላቀ ነበር::

እግዚአብሔር የቀባውና ከእርሱም ሀሳብ ጋር የተስማማ መሪ ለራሱ ወገን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚተርፍ ጸጋና ጥበብ ይሰጠዋል:: በሌሎችም አካባቢ ተፈላጊ የሆነ የሚትረፈረፍ ሕይወት ወይም ምሳሌነት እግዚአብሔር ሊያበዛለት ይችላል:: ስለሆነም ከእግዚአብሔር አሠራር ጋር ተስማምቶ በየትኛውም አገር እግዚአብሔር ወደሚያደርሰው ደረጃ ለመድረስ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ድርብ ኃላፊነት ይሰጠዋል::

### 5 ለመሪ «የቀስት መብዛት» እና የልብስ መገፈፍ የጸጋን መገፈፍ ሊያስከትልበት አይገባም።

ዮሴፍ የሚወደውን ልብስ መልበስ ያልቻለ፤ ሳይወድ ልብሱ የሚገፈፍበት ሰው ነበር። ያጌጠች ልብስ አባቱ ሰጠው (37፡3)፤ ይህችን ያማረች ልብስ ወንድሞቹ ገፈፉት (37፡23)። ወንድሞቹ ከገፈፉት በኋላ ሲሸጡት የገዙት ያለበሱትን (የባሪያ ልብስ) እንደ ለበሰ ወደ ግብጽ እንደ ወረደ መገመት ይቻላል። በጲጥፋራ ቤት ለሥራው የሚመጥን ልብስን ይለብሳል። ይሁን እንጂ በተፈተነ ጊዜ ይህንንም እንኳ ጥሎ ወደ ውጭ ሸሸ (39፡14)። ያንን ልብስ ለብሶ ከኃጢአት ጋር ከመቆየት ይልቅ ራቁትን ለመሆን የመረጠ ጻድቅ ሰው ነው። እንዲሁም ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ በኖረበት ጊዜ የእስረኛ ልብስ ለብሶ እንደኖረ ይታሰባል።

ለታላቅ ዓላማ የተጠራ የእግዚአብሔር ሰው እስከ ጊዜው ድረስ የልብስ መገፈፍ፤ የባሪያ ወይም የእስረኛ ልብስ መልበስ፤ (መገፋት፤ መዋረድ) ይኖርበት ይሆናል። ጊዜው ሲደርስ ግን እግዚአብሔር የክብር ልብስን ያለብሰዋል። የመታሰቡ ጊዜ ሲደርስ ዮሴፍ በመቻኮል ልብሱን ለወጠ (41፡14)፤ ነጭ የተልባ እግር የክብር ልብስ ለበሰ (41፡42)።

ዮሴፍ ብዙ ፍሬ ያለበት የተወደደም ልጅ ስለ ነበር «ቀስት የበዛበት ሰው»[6] ነበር። ቀስተኞች ከውስጥ፤ ቀስተኞች ከውጭ ብዙ አስቸገሩት። በአምላኩ የሚታመነው ዮሴፍ ይህን ሁሉ አሸነፈ እንጂ አልወደቀም። ቃሉ «ነገር ግን ቀስቱ እንደ ጸና ቀረ፤ የእጆቹም ክንድ በያዕቆብ አምላክ እጅ በረታ በዚያው በጠባቂው በእስራኤል አምድ ክንዱን አበረታው» (ዘፍ 49፡24) እንደሚል። በውጭ ሲታይ ባሪያ ነው፤ ምስኪን ነው። በውስጥ ማንነቱ ግን ነፍሱ በጌታ

[6] ቀስት የተቃውሞ፣ የጦርነት፣ የጠላት መውጊያ ምልክት ነው።





የበረታች ነበረች። የመሸነፍና ከጸጋ የመጉደልን ቁልቁለት አልወረደም።

ለአንድ መሪ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋና መክናወን ደስ የማይሰኙ ቀናተኞች ሲኖሩ ልብስንም እስከማስወለቅ ሊደርሱ ይችላሉ። የወንድማቸውን መራቆት የሚፈልጉ ባሉበት ልብስ መገፈፍ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለሆነ ሰው የእግዚአብሔር ሞገስ ልብሱ ይሆናል።

### 6. መሪ የራሱ ሕልም ሳይፈታ የሌሎችን ሕልም ለመፍታት የሚዘጋጅ ነው።

ዮሴፍ በእስር ቤት ለነበሩት የጠጅ አሳላፊና የእንጀራ አበዛ ሕልሞቻቸውን ፈታላቸው። ለሁለቱም ሕልሙን የተረጎመላቸው ትርጉማቸውን ከእግዚአብሔር አግኝቶ ነው። ሕልምን ለመፍታት አልታበየም፤ ይልቁኑ ወደ ሰዎች ጠጋ ብሎ በማነጋገር አደረገው (ዘፍ 40፡7)።



ዮሴፍ ለደረሰበት መከራ እንደ መነሻ የሚቆጠረው ያየው ሕልም ነው። ያየውን ሕልም ለወንድሞቹ ስለ ነገራቸው ጠሉት፤ በጉድጓድም ጣሉት። «ባለ ሕልም» (37፡19) የሚል የቅጽል ስምም ሰጥተውት ነበር።

ያም ቢሆን ዮሴፍ የሌሎችን ሕልም ለመፍታት የራሱ ሕልም እውን እስኪሆን ድረስ አልጠበቀም። የተሰጠውን «የጸጋ ስጦታ» እንደ

መያዣ አልተጠቀመበትም፡፡ «የእኔን ሕልም አስከትፈታ ድረስ የሌሎችን ሕልም ፍቺ አልናገርም» በማለት እግዚአብሔርን አላስቸገረም፡፡

ዮሴፍ ፊቱ የጠቆረን (ያዘነን) ሰው ለመጠየቅና በሚቻለው ለመርዳት የሚወድ ሰው ነበር፡፡ «የራሴ ችግር ሞልቶ ተርፎ» በሚል በራሱ ችግር የማይዋጥ ባለው አቅም ሌሎችን በቅንነት ለማገልገል የተዘጋጀ ሰው ነበር፡፡ የራሱ ሕልም በእግዚአብሔር ጊዜ እንደሚፈጸም የሚያምን መሪ በክረምትና በበጋ በአገልግሎት ቦታው ላይ ይገኛል፡፡

ዮሴፍ በመከራ ውስጥ እያለ የተጣለትን ዝቅ ብሎ በቅንነት ማገልገሉ ያለ ዋጋ አልቀረም፡፡ ይህ ምክንያት ሆኖ እንዲታሰብ ሆነ፡፡ መሪ የአገልግሎት ቦታን ሳይንቅ ባለበት ስፍራ ሁሉ በቅንነት እግዚአብሔርን በመፍራት ያገለግላል፡፡ ስለ ሰዎቹ ማነስና ትልቅነት ሳይሆን በስፍራ ሁሉ የተሰጠውን ጸጋ ይገልጣል፡፡

ዮሴፍ ሕልም የተረጎመው በእስር ቤትና በቤተ መንግሥትም ነበር፡፡ እንዲሁም አገልጋዮች ሰዎችን ባላቸው የሀብት መጠን ሳያበላልጡና የአገልግሎት ቦታን ሳይመርጡ እግዚአብሔር ባስቀመጣቸውና ባሰማራቸው ቦታ ሁሉ በእውነትና በቅንነት ሊያገለግሉ ይገባቸዋል፡፡

## 7. መሪ የእቅድና የተግባር ሰው ነው፡፡

በግብጽ ምድር ሰባት የጥጋብና ሰባት የራብ ዓመታት እንደሚኖሩ ከእግዚአብሔር ከተረዳ በኋላ ዮሴፍ መደረግ ያለበትን አስተዋለ፡፡ ለአሠራሩም አገር አቀፍ ዝርዝር እቅድ በመንደፍ በተግባር ላይ





እግዚአብሔር ለሰጠው መረዳት ምን መደረግ እንዳለበት ለፈረዖን የሰጠው ምክር «ብልህና አዋቂ ሰውን ይፈልግ በግብፅ ምድር ላይ ይሹመው፤ ፈርዖን በምድር ላይ ሹማምንት ይሹም በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ፍሬ በግብፅ ምድር ሁሉ ከአምስተኛው እጅ አንደኛውን ይውሰድ፤ ይከማች፤ ስንዴውንም ከፈርዖን እጅ በታች ያኑሩ፤ እህሎችም በከተሞች ይጠበቁ» (ዘፍ 41፡33-36) በማለት ነበር፡፡ በዚህ የእቅድ ሀሳብ ውስጥ ምን፤ ለምን፤ ማን፤ መቼ፤ የት፤ ስንት፤ እንዴት፤ የሚሉ የእቅድ ዝግጅት ዝርዝር ክፍሎች ተጠቃለዋል፡፡

ዮሴፍ ወደ ሹመት ከመጣም በኋላ ለእቅዱ የአፈጻጸም መርሃ ግብር አወጣ፡፡ በምድሪቱ ለየቦታው ተስማሚ የሆነ ዝግጅት ያደረገና ትተራዎችንም ያዘጋጀ ብልህ መሪ ነበር፡፡ በዝግጅቱም የግብጽን ምድር ሁሉ ዞሮ በማየት ለሰባት ዓመት እህል ሰበሰበ፤ በየከተሞቹ ጎተራን አዘጋጀ፤ እህሉ እንዲከተትና እንዲከማች አደረገ፡፡

በእቅድ ሥራ ነባራዊ ሁኔታውን መመልከት (ዐውዱን ማወቅ) እና በቂ መረጃ መሰብሰብ ያንንም በሥራ መተርጎም አስፈላጊ መሆኑን ከዮሴፍ አሠራር እንማራለን፡፡ እንዲሁም መልካም አስተዳደር ከመሪዎች ይጠበቃል፡፡ ዮሴፍ እህልን የመግዛትና የማስተዳደርን ኃላፊነት የተወጣው በታማኝነት ነበር፡፡

ጠንካራ መሪዎች ከደካማ፤ ጎበዝ መሪዎች ከመለስተኛ፤ የሚለዩበት አንዱ ምልክት ጎበዝ መሪዎች የሚያልሙና የሚያስቡ ብቻ ሳይሆኑ እቅድን በተግባር በመተርጎምም ብርቱ መሆናቸው ነው፡፡ ጎበዝ መሪዎች እቅድን የሚነድፉ ብቻ ሳይሆኑ እንደ ዮሴፍ በተግባር የሚተረጉሙም እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ለጎበዝ መሪዎች ሀሳብና ተግባር፤ ራእይና አስተዳደር የተያያዙ ናቸው፡፡

## 8. የእግዚአብሔርን መልካምነት የተረዳ መሪ፤ መከራን ይረሳል፤ ይቅርታ ማድረግ ያውቃል።

ዮሴፍ ወደ ሹመት ከመጣ በኋላ ወንድሞቹ ወደ እርሱ ሲመጡ ድሮ ያደረጉበትን ጭከና በማሰብ ለመበቀል በሚያስችለው ሁኔታ ላይ ነበር። በሰው አስተሳሰብ ሁሉንም ሊያስገድላቸው ሥልጣን ነበረው። ዮሴፍ ግን ወንድሞቹ በመጡ ጊዜ ይቅርታ አደረገላቸው (45፡4-5)። የሚበሉትንም ሁሉ ሰጣቸው፤ ከራብ ለማምለጥ ወደ ግብጽ እንዲመጡም ጋበዛቸው።

ወንድሞቹ ከ20 ዓመት በኋላ ዮሴፍን ሲያገኙት እርሱን መበደላቸውንና ነፍሱ ተጨንቃ ሲማጠናቸው አለመስማታቸው ትዝ ይላቸዋል (42፡21)። ዮሴፍ ይቅርታ ካደረገላቸው ከ17 ዓመታት ያህል በኋላም ቢሆን ወንድሞቹ ግን ይቅርታ ይጠይቁት ነበር። ያደረጉት ኃጢአት ሁልጊዜ በውስጣቸው ይወቅሳቸው ነበር። መጽሐፍ «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» (ምሳ 28፡13) እንደሚል።

ዮሴፍ የወንድሞቹን ኃጢአት ይቅር በማለት ብቻ አላበቃም። እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወት ያደረገውን መልካም ነገር ከመመስከር ዝም አላለም። የእግዚአብሔር ሰው ዮሴፍ ወደ ሕይወቱ መጨረሻ ሲደርስ «እናንተ ለክፉ አሰባችሁት እግዚአብሔር ግን ለመልካም አደረገው» (ዘፍ 50፡20) በማለት የእግዚአብሔርን ታላቅነትና መልካምነት ተናገረ። እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ውስጥ መልካምን ነገር አወጣ። ሁኔታው ለመልካም የሆነለት (የተቀየረለት) ዮሴፍ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ክፉ አድራጊዎችም ናቸው። ክፉ ያደረጉበት ሰዎችም በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር የዮሴፍን መከራ እንደ ምክንያት ተጠቀመበት።





እግዚአብሔር ኤልሻዳይ (ሁሉን የሚችል አምላክ) ነውና ክፉን ነገር ወደ መልካም መለወጥ ይችላል። ሰዎች ክፉን ሲያደርጉ የሚያደርጉት ነገር በእርግጥም ክፉ ነው። ለምሳሌ ዮሴፍ መጠላቱ፤ ልብሱ መገፈፉ፤ ወደ ጉድጓድ መጣሉ፤ መሸጡ ሁሉ ክፉ ነገር ነው። እግዚአብሔር ግን ክፉውን ወደ መልካም ለወጠው።

እዚህ ላይ ልብ እንበል! ለዮሴፍ መከራ ተጠያቂው ማን ነው? እግዚአብሔር ጻድቅ አምላክ ክፉውን ነገር ወደ መልካም መለወጥ ይችላል። እግዚአብሔር በዮሴፍ ላይ የመጣበትን ክፉ ነገር ለመልካም አሰበው፤ ማለትም ወደ መልካም ለወጠው እንጂ በቅንዓት ክፉ አሰበው ድርጊቱን የፈጸሙትማ ወንድሞቹ ናቸው (45፡4-9፤ 50፡20)። ስለሆነም ለዮሴፍ መከራ ተጠያቂዎቹ ክፉ አድራጊዎቹ ወንድሞቹ ናቸው።

በዮሴፍ ላይ የሆነው መከራ ከወንድሞቹ ቅናት የመጣ የአመፅ ሥራ ነበር (ሐዋ 7፡9)። ወንድሞቹ ያደረጉበት ሁሉ የጥላቻቸው መግለጫ ነው። ወንድሞቹ ያሰቡት ክፉ ነበር፤ ድርጊታቸውም ክፉ ነው። ክፉም እንዳደረጉ አውቀው ሲሳቀቁ የኖሩ እነርሱው ናቸው። እግዚአብሔር ደግሞ በራሱ ሚዛን ለክፉ አድራጊዎች ብድራትን ይከፍላል።

እግዚአብሔር ጻድቅ አምላክ ስለ ዮሴፍ መከራ ተጠያቂ አይደለም። እግዚአብሔር ሊያደርግ የወደደውን ሁሉ በመረጠው መንገድ ሊፈጽመው ይችላል። የእግዚአብሔር ታላቅነትና መልካምነት የሚገለጠው ሰዎች ለክፉ ያደረጉትን ለበጎ መቀየሩና የራሱንም ዓላማ መፈጸሙ ነው። ይህ የእርሱን ቸርነትና አምላክነት ይገልጣል።

በሌላም ቦታ ቃሉ «እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደ ሀሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» (ሮሜ 8:28) ይላል:: እናስተውል:- ነገር ሁሉ በጎ ነው፤ ወይም ነገር ሁሉ ለበጎ ነው አላለም፤ ሁሉም ነገር በጎ አይደለምና:: እግዚአብሔር ግን በታላቅነቱ ለክፉ የመጣውን ወደ መልካም መለወጥ ይችላል:: እርሱ ከበላተኛ መብልን፤ ከመራራ ነገር ጥፍጥን ያወጣል (መሳ 14:13-14)::

እንግዲህ እግዚአብሔርን የሚያውቅ መሪ እርሱ በሕይወቱ ያደረገውን እያሰበ የሚያመሰግን፤ የበደሉትንም ይቅር የሚል ነው::

## 9. የእግዚአብሔርን አሠራር የሚያስተውል መሪ ክብርን ለእርሱ ይሰጣል::

በከነዓን ራብ እንደሚሆንና የያዕቆብ ልጆች ወደ ግብጽ እንደሚመጡ እግዚአብሔር አስቀድሞ አይቶአል:: መጽሐፍ «በፊታቸው ሰው ላከ ዮሴፍ ለባርነት ተሸጠ» (መዝ 105:17) እንደሚል የያዕቆብ ዘር በራብ እንዳይሞት አስቀድሞ እግዚአብሔር ዮሴፍን ከእነርሱ በፊት ላከው:: በከነዓን ራብ የሆነው ዮሴፍ ሕልምን ካየ ከ22 ዓመታት ያህል በኋላ ነበር::

ዮሴፍ ወደ ግብጽ የተላከበት አንዱ ምክንያት ያዕቆብና ልጆቹ በራብ እንዳይሞቱ እህልን እንዲያዘጋጅላቸው ነበር ማለት ነው:: ወደ ግብጽ የሄደበት መንገድ ግን የባርነት መንገድ ነው፤ ያውም በወንድሞቹ በመሸጥ:: በእግዚአብሔር ዓይን ደግሞ ዮሴፍ ወደፊት ለወንድሞቹ የሚሆነውን ቀድሞ እንዲያሰናዳ ወደ ግብጽ የተላከ ሰው ነው:: የተላከበትም ምክንያት ለሸጡት (ለሚሸጡት) ወንድሞቹ ስንዴ በመስጠት በሕይወት እንዲቆዩ ለማድረግ ነው (ሐዋ 7:9፤11)::





በሰው ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ጥሪ አፈጻጸሙ መቼና እንዴት መሆኑ በቀላሉ ላይታወቅ ይችላል:: የዮሴፍ ሕልሙ (ጥሪው) መቼና በምን መንገድ እንደሚፈጸምም አላወቀም:: የደረሰበት ነገር ሁሉ ለምን እንደ ደረሰበት ከመነሻው አልተረዳውም:: ሕልምን የሰጠ እግዚአብሔር ግን ይህን ሁሉ ያውቃል::

በሬ እንኮቱን ለቀንበር እንደሚሰጥ፤ ግመልም ለመጫን ፈቃደኛነቱን በመንበርከክ እንደሚያሳይ የዮሴፍም ሕይወት ለጌታው ለእግዚአብሔር የታዛዥነት መንገድ ነበር:: ከዚህ የሕይወት መንገድ ውስጥ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ተገኘ:: የዮሴፍ ሕልም ከፍ ከፍ የማለት ሕልም ነበር:: የተፈጸመው በጉድጓድ ውስጥ በመጣል፤ ለባርነት በመሸጥ፤ በመፈተን፤ በመታሰር በኩል ነው::

እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ እስኪደርስለት ድረስ በመጠባበቅ መከራ በበዛበት መንገድ የሚጓዝ ሰው ሌላው እንደሚለው «ባሪያ» ሳይሆን እግዚአብሔር እንዳሰበለት «መልእክተኛ» ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው እግዚአብሔር በሕይወቱ ሊሠራ የሚወደውን አገልግሎት አሳምሮ ይሠራና ይፈጽም ዘንድ ራሱን ያቀረበ ሰው ነው::

ዮሴፍ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ሲገነዘብ ከአባቱ ቤት የወጣው ለባርነት በመሸጥ ቢሆንም ዓይኖቹን ከሰው ላይ አንስቶ እይል ፊንታው በሆነ እግዚአብሔር ላይ አደረገ:: ስለሆነም እግዚአብሔር ወደ ግብጽ «ሰድዶኛል፤ ...ላከኝ ...አደረገኝ» (ዘፍ 45:5-8-) አለ:: እንዲሁም በረከቱን በመቁጠር «አስረሳኝ ...አፈራኝ» (41:51) በማለት ክብርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል::

ዮሴፍ እግዚአብሔርን የመፍራቱ ሌላው መገለጫ ሁልጊዜ ክብርን ለእግዚአብሔር መስጠቱ ነው:: ለፈርዖን ሕልምን ከፈታለት በኋላ

«ይህ በእኔ አይደለም እግዚአብሔር ግን ለፈርዖን በደኅንነት ይመልስለታል» (41፡16) ብሎ ሲናገር በፈርዖን ፊት ያገኘውን ከበሬታ ተጠቅሞ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ አልወደደም። እግዚአብሔርን በሁሉ ሁኔታ ለማክበር የቆረጠ ታማኝና ትሑት ሰው ነበር። ይህ መሪዎች መቼውንም ቢሆን ሊዘነጉት የማይገባ ትምህርት ነው።

## 10. መሪ የበረከት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚገነዘብ የእምነት ሰው ነው።

ከ13 ዓመት በፊት በግብጽ የባሪያ ገበያ ላይ የተሸጠው ዮሴፍ አሁን በ1885 ዓ.ዓ አካባቢ በምድሪቱ ከፈርዖን ቀጥሎ ያለ ባለሥልጣን ሆነ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ ከግብጽ ውጪ እህል ለመግዛት ከሚቀርቡለት ጥያቄዎች የተነሣ በሌሎች አገሮች የታወቀ ዓለማቀፋዊ ባለ ሥልጣን ሆነ።

በግብጽ ምድር ከፍ ባለ ሥልጣን ላይ የነበረ በመሆኑ ልጆቹ ጥሩ ኑሮ እንደሚኖራቸው ቢገመትም ሰማያዊ በረከትን አብልጦ ይፈልግ ነበር። ልጆቹንም የእግዚአብሔር ተስፋ ካለው ሕዝብ ጋር አዛምዶ ለማሳደግ የፈለገ ሰው ነው። ወደ አባቱ አቅርቦ እንዲባረኩ ሲያደርግ ዮሴፍ የአባቱን አምላክ ማምለክ እንደቀጠለና ልጆቹም በዚህ እምነት በመቀጠል እንዲባረኩ መፈለጉን ያሳየናል። ዮሴፍ የእግዚአብሔርን በረከት ለልጆቹ አወረሰ።

ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ስለባረከበት ሁኔታ አንድ ነገር ልብ እንበል። ሁልጊዜም መጀመሪያ የሚባረክና መጀመሪያ ድርሻውን የሚያገኝ በኩሩ እንደሆነ በአጠቃላይ የታወቀ ሆኖ ሳለ ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ሲባርክ ይህንን መስመር አልተከተለም። እጆቹን በማመሳቀል (ወይም በማስተላለፍ) ቀኝ እጁን ታናሽ በነበረው





እናያለን። ታናሹ የበላይነትን ወይም የታላቅነትን ክብር በመባረክ አገኘ።

መንፈሳዊ አሠራር በተፈጥሮ ከሚታየው ልምድ በላይ ነው። ሁለቱም የዮሴፍ ልጆች ተባርከዋል። ሁለቱም የወገን መሪዎች ሆነዋል። ነገር ግን ያዕቆብ ሲባርካቸው እንዳለው ኤፍሬም ከምናሴ የበለጠ ሆኖአል። እግዚአብሔር አዋቂ ነው። እንደ እውቀቱና እንደ በጎ ፈቃዱ ሁሉን ያደርጋል። በተፈጥሮ ሁልጊዜ ትልቁ (በኩሩ) ይበልጣል። እግዚአብሔር የባረከው ግን ታናሽም ቢሆን እርሱ «በኩር» ይሆናል።

የእምነት ሰው አሁን ከሚታየው ባሻገር ወደፊት ሊሆን ያለውን አሻግሮ የሚያይ፤ የተስፋን መፈጸም የሚጠባበቅ ሰው ነው። እምነት እግዚአብሔር እንደተናገረው ያደርጋል ብሎ ተስፋ በማድረግ መራመድ ነው። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ሰዓት ከግብጽ እንደሚወጡ በመረዳት አጥንቱን ከእነርሱ ጋር እንዲያወጡ በእምነት የተናገረ ሰው ነው። ይህም ደግሞ ሆኗል (ዘጸ 13፡19፤ ኢያሱ 24፡32፤ ዕብ 11፡22)።

በማጠቃለል፡- ዮሴፍ መልካም የአገልጋይነት ባሕርይ ገና ከወጣትነቱ ጀምሮ የታየበት ሰው ነበር። ወንድሞቹ ወደሄዱበት ቦታ ሁሉ ፈልጎ በማግኘት ለአባቱ ታዛዥነቱን፤ ለወንድሞቹም የነበረውን ፍቅር ገልጦአል።

እግዚአብሔር ዮሴፍን ለመሪነት ያሰለጠነበትና ያዘጋጀበት መንገድ ልዩ ነው። የመሪነት ማሰልጠኛ ማዕከል (ትምህርት ቤት) ባልነበረበት ዘመን ባሪያ ሆነ በሚያገለግልበት ምድር በቀጥታ ለመሪነት የተመረጠ ሰው ነበር።

በአጠቃላይ የሴፍ የእግዚአብሔርን ባሕርይና አሠራር የተረዳ፤ ክፉውን ወደ መልካም መቀየር የሚቻለው መሆኑን ያወቀ እግዚአብሔርን እያከበረ ወደ አባቶቹ የተሰበሰበ ታላቅ መሪ ነበር:: በአንድ ሰው የሴፍ መከራን መታገስ ምክንያት የተሰፋው ሕዝብ በራብ ዘመን የሚበላውን አገኘ::

የሴፍ በሚነድ ምድጃ ውስጥ ሲያልፍ መልኩን ያልቀየረ መሪ ነው::





## ምዕራፍ 2

# ሙሴ

ሙሴ በ1400 ዓ.ዓ. አካባቢ የኖረ በእግዚአብሔር ትእዛዝ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ያወጣና ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራ ታላቅ መሪ ነው:: የሙሴን የሕይወት ዘመን በሦስት አርባ ዓመታት ከፍሎ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል::

### የመጀመሪያዎቹ አርባ ዓመታት

ሙሴ የተወለደው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውና ከ300 ዓመታት በላይ ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ ሊፈጸም በተቃረበበት ዘመን ነበር:: ሙሴ ከሌዊ ወገን ሲሆን አባቱ እንበረም እናቱ ደግሞ ዮካብድ ይባሉ ነበር (ዘጸ 6:20፤ ዘኁ 26:58-59):: የአሮንና የማርያም ወንድም ነው::

ሙሴ የተወለደበት ዘመን በግብፅ ምድር ይኖሩ የነበሩ እስራኤላውያን መብዛት ያሰጋው ፈርዖን ወንድ ሆኖ የሚወለድ ዕብራዊ ሁሉ እንዲገደል ትእዛዝ ባወጣበት ዘመን ነበር:: ሕፃኑን ሙሴን ወላጆቹ ከሦስት ወር በላይ ሊሸሽጉት ባልቻሉ ጊዜ (ዕብ 11:23) በቅርጫት አድርገው ወደ ወንዝ ጣሉት:: ግብጻዊቷ የፈርዖን ልጅ አንስታ አሳደገችው (ዘጸ 2:1-10)::

የሙሴ ወላጅ እናት እስራኤላዊት አሳዳጊው ደግሞ ግብጻዊት ነበሩ:: የሙሴ እናት በቤቷ ልትሸሽገው ያልቻለችውን ልጇን እየተከፈላት (ዘጸ 2:9) በግልጽ አሳደገቺው:: የተወለደው በባርነት ከሚኖሩ ዕብራውያን ሲሆን ያደገው በቤተ መንግሥት ውስጥ

በንጉሥ «ልጅነት» ነበር:: ፈርዖን ሊያስገድላቸው ከሚፈልጋቸው የዕብራውያን ልጆች መካከል አንዱ በራሱ ቤተ መንግሥት ውስጥ አደገ (ዘፍ 2:10)::

በፈርዖንም ቤት ሲያድግ የግብጽን ሁሉ ጥበብ ተማረ (ሐዋ 7:22):: ሙሴን ወላጆቹ ወደ ወንዝ ሲጥሉት «ሊሸሽጉት» ስላቃታቸው ነበር:: በሰው አእምሮ «አጋጣሚ» የሚመስል ነገር እግዚአብሔር ደግሞ የዘላለም ሀሳቡን የፈጸመበት እንዲህ ዓይነት ድንቅ ጥበቃና አስተዳደግ «ሃሳቤ ከሃሳባችሁ ...» (ኢሳ 55:9) የሚለውን ያሳስበናል::

## ሁለተኛዎቹ አርባ ዓመታት

የሙሴ የመጀመሪያው አርባ ዓመት ዕድገቱ በቤተ መንግሥት ውስጥ የግብጽን ጥበብ እየተማረ ሲሆን ሁለተኛው አርባ ዓመት ደግሞ በምድረ በዳ በበግ ጥበቃ ነበር:: በሁለተኛው አርባ ዓመት ሙሴ ዘመኑን ያሳለፈው ከወገኖቹም ሆነ ከንጉሡ ፊት ርቆ በምድያም ምድረ በዳ ነበር:: በዚያ በሄደበት አገር የዮቶርን ልጅ ሲፓራን አገባ (ዘጸ 2:21):: ሁለት ልጆችን እግዚአብሔር ሰጠው:: አንደኛውን «በሌላ አገር ስደተኛ ነበርሁ» ሲል ጌርሳም አለው:: ሁለተኛውንም «የአባቴ አምላክ ረዳኝ ከፈርዖንም ሰይፍ አዳነኝ» ሲል አልዓዛር ብሎ ጠራው (ዘጸ 18:3-4)::

በቤተ መንግሥት ውስጥም ሆነ በምድረ በዳ እግዚአብሔር ለወደፊት ሕዝብን የመምራት አገልግሎቱ የሚጠቅመውን እያስተማረውና እያሰለጠነው ነበር:: በጎችን በምድረ በዳ መጠበቁ በምድረ በዳ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መልካም እረኛ ሆኖ ለመምራት በብዙ ያግዘዋል:: እርሱም በግሉ የምድረ በዳን ኑሮና መንገድ ይለማመዳል፤ ይሰለጥናል::





የእግዚአብሔር የመሪነት ጥሪ በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ ሙሴ የመጣው በሁለተኛው አርባ ዓመት መጨረሻ ላይ ነው:: በሁለተኛው አርባ ዓመት መጨረሻ አንድ ቀን ሙሴ የዮቶርን በጎች እየነዳ «ወደ ምድር በዳ ዳርቻ» መጣ (ዘጸ 3:1):: ያ ቀን ለሙሴም በምድያም ምድር የስደት ኑሮው ዳርቻ ሆነለት:: በዚያ ቦታ እግዚአብሔር ለሙሴ ያለውን ሀሳብ ገለጠለት::

የእስራኤልን ከግብጽ መውጣት ለአብርሃም ተስፋ ከሰጠበት ከ400 ዓመታት በፊት ጀምሮ እግዚአብሔር ሁኔታውን ሁሉ እያዘጋጀ ነበር:: ሙሴንም ከ80 ዓመት በፊት ጀምሮ እየተንከባከበውና ለመሪነት ኃላፊነት እያዘጋጀው ነበር:: በዚህ ዝግጅት የሙሴን ወላጆች፤ ሕፃኑ ሙሴ እንዳይገደል ያደረጉ አዋላጆችን፤ የፈርዖንን ልጅ፤ የሙሴን እህት ሁሉ ተጠቅሟል:: አሁን ጊዜው ደረሰ::

## ሦስተኛዎቹ አርባ ዓመታት

ሦስተኛው አርባ ዓመት የሙሴ የመሪነት አገልግሎት ዘመን ሲሆን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በምድረ በዳ የቆየባቸው ዓመታት ናቸው:: የሚጀምረውም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድ ነገር ግን ሳይቃጠል ካየበት ጊዜ ነው (ዘጸ 3:2):: እየነደደ የማይቃጠለውን ቁጥቋጦ ለማየት ሙሴ ወደ ቁጥቋጦው ቀረበ:: እግዚአብሔርም ሙሴን በስሙ «ሙሴ ሙሴ ሆይ» ብሎ ጠራው (ዘጸ 3:4):: ሕዝቡን ከግብጽ ያወጣ ዘንድ ተልዕኮ ሰጠው (3:10)::

ሙሴ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሪነት (እረኝነት) ጥሪ ከደረሰው በኋላ ስለ ራሱ ታናሽነት በማሰብ በተደጋጋሚ እግዚአብሔርን ይጠይቃል:: የእግዚአብሔርም መልስ ለሙሴ የመጣለት ጥሪ ከጠሪው ማንነት የተነሣ እንጂ ከተጠሪው ብቃት አለመሆኑን የሚያስገነዝብ ነው:: በመጨረሻም ጥሪውን ተቀብሎ «የእግዚአብሔርን በትር ይዞ» (4:20) ወደ ግብጽ ተመለሰ::

ሙሴ በፊቱ የተዘረጋው- ሕዝብን በሰላማዊ መንገድ ከገዥዎቻቸው እጅ ነፃ አውጥቶ የተስፋይቱን ምድር የማውረስ ተግባር እጅግ ትልቅ ነው:: ሁለት ሚሊዮን የሚያህሉትን «በባርነት» ያሉ እስራኤላውያን ከበረታ የንጉሥ አገዛዝ እጅ ነፃ የሚያወጣቸው እግዚአብሔር እንዲናገር የሚሰጠውን ቃል ለፈርዖን በመናገር ብቻ ነው:: ሙሴ ያለው ኃይል ‹እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑ› ነው:: ሙሴ በእጁ የያዘው «የእግዚአብሔርን በትር» ነው::

ሙሴ ታላቅ የሕዝብ መሪ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያነብ ሰው ሁሉ ግልጽ ነው:: ከዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር ባሪያ ሕይወትና አመራር የምንማረውን አጠር ባለ መንገድ በማጠቃለል እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል::

### 1. መሪ ምርጫውን የሚያውቅና እምቢ ማለት የሚችል የእምነት ሰው ነው::

ሙሴን ያሳደገችው የፈርዖን ልጅ በመሆኗ እርሱ የፈርዖን የልጅ ልጅ ሊባል በቻለ ነበር:: ይህም እንደ ሰው አስተሳሰብ የሚያጓጓና ልብን የሚያማልል ምኞት ነው:: በቦታው የሚያስገኘው ክብር፤ ጥቅምና «ደስታ» ከፍተኛ በሆነ ነበር:: ሆኖም የሙሴ ታላቅነት ጊዜያዊውን ከዘላቂው (ከዘላለማዊው) መለየትና ዘላቂውን ለመምረጥ መወሰኑ ነው:: ዘላለማዊውን መለየት የቻለው «አትኩሮ/ በርቀት»[7] በመመልከቱ ነው:: በርቀት ያለውን መመልከት የሚቻለው በእምነት ነው:: ቃሉ እንደሚል:-

[7] "...turning his eyes away from other considerations, he fixed them on the (eternal) recompense" (Heb_11:39-40). JFB. "...either the deliverance of the Israelites from their bondage, which he judged a sufficient recompence for all his afflictions and reproaches he endured, as the Apostle Paul did for the elect's sake, for the sake of Christ's body the church, Col_1:24 or the enjoyment of the land of Canaan, promised





«ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እንቢ አለ፤ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና» (ዕብ 11:24-26)::

ሙሴ አትኩሮ የተመለከተውን ሲመርጥ የነበረውን የክብር መጠሪያ ስምና የሚያስገኘውን ክብር እምቢ ማለቱ ነበር:: ይህ በሕይወት ሊደረግ የሚችል «ሁሉን ትቶ የመከተል» ትልቅ ውሳኔ ነው:: ሙሴ ይህንን ምርጫ ያደረገው ሕዝቡን ከባርነት እንዲያወጣ ለመሪነት ከመጠራቱ በፊት ነበር:: ይህም የሆነው «ስለ ክርስቶስ መነቀፍን»[8] በመምረጡ ነው:: ከዚህ ውሳኔው የተነሣ ሙሴ ከሕዝቡ ተለይቶ ወደ ምድያም ኮበለለ እግዚአብሔር እስኪያስበውም ድረስ በዚያ ኖረ::

for an inheritance to the seed of Abraham; or the enjoyment of God's presence among his people, who is their shield, and exceeding great reward; or rather eternal glory, which is the reward of the inheritance, and is a reward of grace, and not of debt; this he had respect unto, looked for, and believed he should enjoy; so that his faith was of things unseen; " Gill.

[8] "The reproach of Christ - That which he bore for believing in the Messiah to come, and acting accordingly", WEN. "that is, the reproach which falls on the Church, and which Christ regards as His own reproach, He being the Head, and the Church (both of the Old and New Testament) His body. Israel typified Christ; Israel's sufferings were Christ's sufferings (compare 2Co.1:5; Col.1:24). As uncircumcision was Egypt's reproach, so circumcision was the badge of Israel's expectation of Christ, which Moses especially cherished, and which the Gentiles reproached Israel on account of. Christ's people's reproach will ere long be their great glory." JFB.

ክርስቶስን ለመከተል መወሰን በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የምርጫ ውሳኔን ያስከትላል፡፡ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ ከማንኛውም «በኃጢአት ከሚገኝ» ባለጠግነትና ክብር ሁሉ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት ነው፡፡ ይህ ባለጠግነት በገንዘብና በንብረት መጠን ላይለካ ይችላል፡፡ ግን ብድራት (ዘላለማዊ ዋጋ) አለው፡፡

እንግዲህ መሪ የምርጫ ሰው ነው፡፡ በሕይወቱ የሚመርጠውን ለይቶና አጥርቶ ማወቅ አለበት፡፡ የእግዚአብሔርን ሀሳብ በሕይወቱ ለማገልገል በመምረጥ ከዚህ ጋር አብሮ የሚመጣውን መነቀፍና መከራ መምረጥ ነው፡፡ ምርጫው ከእግዚአብሔር ሕዝብና ወገን መቆም ነው፡፡ የሕዝቡ ክፍል (አካል) ነውና የእግዚአብሔር ሕዝብ መከራና ችግር ውስጥ እያለ ለራሱ እስኪተመቸው ድረስ ተለይቶ አይኖርም፤ ተድላን አይመርጥም፡፡ መሪ እግዚአብሔር ሕዝቡን ባሰበና ደስ ባሰኘ ጊዜ አብሮ ከሕዝቡ ጋር ደስታን በመካፈል ሕዝቡን የሚመስል ሰው ነው፡፡

የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመውደድ ከሕዝቡ ጋር በአብሮነት ለማዘንና ለመደሰት መወሰን አንድ ሰው ወደ መሪነት ቦታ ከመጣ በኋላ ብቻ የሚያሳየው ባሕርይ ሊሆን አይገባም፡፡ ይህ ቀድሞውኑ በልቡ ሊኖር የሚገባው የውስጥ ግፊት ነው፡፡

## 2. መሪ በእግዚአብሔር ጊዜ የሚሾም ነው፡፡

ሙሴ መሪ ሆኖ በእግዚአብሔር የተሾመው በ80 ዓመት ዕድሜው ሲሆን የመሪነት ሽከሙ ይታይ የነበረው ግን ገና በአርባ ዓመት ዕድሜው አካባቢ ነበር፡፡ ራሱን ወደ ወንድሞቹ ወደ እስራኤላውያን በማቅረብ ለተገፋው ሲበቀል ሸከሙን ይገልጥ ነበር (ሐዋ 7፡24)፡፡ እንዲሁም «ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም» (ሐዋ 7፡25)፡፡





ከዚህ ጊዜ በኋላ ሙሴ ለሚቀጥሉት አርባ ዓመታት የኖረው ከወንድሞቹ ተለይቶ በምድረ በዳ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ለመሆኑ ያ በልቡ የነበረው መነሳሣት ከየት መጣ? ከዚያስ በኋላ አርባ ዓመት ሙሉ ሙሴ ምን ሲያደርግ ነበረ? ለዚህ ሁሉ ዘመን የመሪነት ሸከሙስ ምን ሆኖ ይሆን? ብለን ለመጠየቅ እንችላለን፡፡

በመጀመሪያ ምንም እንኳ «ወንድሞቹ ባያስተውሉም እርሱ ግን «ወንድሞቹ ...የሚያስተውሉ» እንዲሁም «እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው» ይመስለው ነበር፡፡ ይህም ማለት ወንድሞቹን ከባርነት ለመታደግ እግዚአብሔር እርሱን እንደሚጠቀም በልቡ የተረዳው ነገር መኖሩን እናያለን፡፡ ወንድሞቹም «አንተን በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማነው?» (ሐዋ 7፡27) ሲሉት የሹምና ፈራጅ ሁኔታን (ድርጊትን) አይተውበት ነበር፤ ነገር ግን አልተቀበሉትም (7፡35))፡፡ የእነርሱ ጥያቄ ማን ነው የሾመህ የሚል ነው? ጥሪው ቢኖረውም የሚላከበት ጊዜ ግን ገና አልደረም ነበር፡፡

ከአርባ የስደትና የመከራ ዓመታት በኋላ የእግዚአብሔር ሰዓት ሲሞላ ሙሴን ወደ ካዱት (ወዳልተቀበሉት ወንድሞቹ) «እግዚአብሔር ሹምና ቤዛ አድርጎ ላከው» (7፡35)፡፡ የእግዚአብሔር ሰዓት ሲሞላ ጥሪው የበለጠ ግልጽ ሆኗል፡፡ በመልካም ለማስተዳደር (ሹምና ፈራጅ[9]) የተሾመ ብቻ ሳይሆን ነፃ ለማውጣትም (ሹምና ቤዛ[10]) ሆኖ ነው የተሾመው፡፡ አሁን የእግዚአብሔር ጊዜ ስለደረሰ የሙሴ የመገለጫው ጊዜ ነው፡፡ ወንድሞቹም እንደ ቀድሞው አልተቃወሙትም፡፡

[9] a ruler and a judge (KJV)

[10] a ruler and a deliverer (KJV)

እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ሰዓት በሚመለከት ክርስቲያኖች ሁሉ በተለይም መሪዎች ሊያስተውሉት የሚገባ ትልቅ ቁም ነገር አለ:: እግዚአብሔር ኃጢአትን ለመቅጣት ጽዋ እስኪሞላ እንደሚታገስ (ዘፍ 15፡16)፤ ለንስሐም ጊዜ እንደሚሰጥ (ራእ 2፡21) እንዲሁ ሰውን ወዳሰበው ቦታ ለማድረስና ለመሾም የራሱ ሰዓት አለው:: ዳዊት በዙፋን ላይ የተቀመጠው እንደተቀባ ወዲያውኑ አልነበረም:: ቢያንስ 15 ዓመት ጠብቋል:: በተቀባበትና በዙፋን በተቀመጠበት መካከል ያሉትን አብዛኛዎቹን ዓመታት ያሳለፈው ደግሞ በስደት ነበር::

ብዙ መሪዎች (አገልጋዮች) ግን በዚህ ነገር ይቸገራሉ:: የአገልግሎት ጥሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከመጣ በኋላ ወደተባለው አገልግሎት እስኪመጡ ድረስ በመሀከል ረጅም «የምድረ በዳ ዓመታት» ሊኖሩ ይችላሉ:: በዚህ ዘመን ከወንድሞች ተቃውሞና ብርቱ ስደትም ሊኖር ይችላል:: የእግዚአብሔር ጥሪ ግን ቢዘገይ እንጂ አይከስምም:: ፍሙ ቢዳፈን እንጂ አይከስልም:: መጀመሪያ እሳቱን የለኮሰ እግዚአብሔር በጊዜው እፍ ሲልበት ማንም ሊያግደው በማይችል ሁኔታ እንደ ሰደድ እሳት በርቶ ደምቆ ይወጣል:: ስለዚህ ለአገልግሎት መቀባት አንድ ነገር ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቶ ያ ቅባት የሚገለጥበትን ጊዜ መጠባበቅ ደግሞ ሌላ ነው::

## 3. መሪ ከእግዚአብሔር እየሰማ ሕዝብን የሚዳኝና የሚያስማራ ነው::

የሙሴ አመራር አንድ ትልቁ መታወቂያው ወደ እግዚአብሔር በመጮኽና ምሪትን በመቀበል ያደረገው አመራር ነው:: ወደ እግዚአብሔር ጮኽ (ጠየቀ) የሚለው ቃል ከዘጸአት እስከ ዘዳግም ባሉት መጻሕፍት ከአርባ ጊዜ በላይ ተደጋግሞ እናየዋለን:: ለምሳሌ





በዘጸ 17፡4 ከሕዝቡ ችግር ጥያቄ ሲመጣ ሙሴ ያንን ጥያቄ ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ (በመጮኽ) መልስን ፈለገ::

ሙሴ በራሱ ችሎታ፤ ልምድና ማስተዋል ላይ የማይደገፍ በእግዚአብሔር ለመመራት የመረጠ መሪ ነበር:: አዘውትሮም ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ይወዳል:: ይህን የኑሮው ክፍል አድርጎታል:: እግዚአብሔርም ፊት ለፊት ይናገረው ነበር:: ሙሴ መንገድ ከጀመረ በኋላም ለቀሪው ጉዞው «መንገድህን አሳየኝ» (ዘጸ 33፡13-15) ብሎ እግዚአብሔርን የሚጠይቅ መሪ ነው:: ሙሴም «መንገዱን አወቀ» (መዝ 103፡7) ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር ለሙሴ መንገዱን አሳይቶታል:: ብቻ ከግብጽ ያስወጣንና ባሕሩንም ይከፈልልን እንጂ «የተቀረውን ጉዞ እኛ እንችለዋለን፤ ከቸገረን እንጠራሃለን» በሚል ዓይነት ልብ ያልተያዘ ሰው ነበር:: የየዕለት አካሄዱ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር የተስማማ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ሰው አስተዋይ መሪ ነው::

ሙሴ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር ተስማምቶ ለመኖር የመረጠ ታላቅ መሪ ነው:: ለሕዝቡ ዳኝነትና ፍርድን ሲያደርግ በግልጽ በቃሉ የተጻፈ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በአቅራቢያ አንቀጽ ውሳኔ ላለመስጠት የሚጠነቀቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ነበር:: በሰንበት ቀን እንጨት ሲለቅም ያገኙትን ሰው በመጽሐፍ ምን እንደሚደረግ ተጽፎ ስላልተገኘ እግዚአብሔር እስኪናገር ድረስ በግዞት እንዳኖረው በዘኁ 15፡34 እናነባለን:: ታላቅ መሪ እግዚአብሔር አብሮት እንዲሆንና እንዲመራው የሚለምን ሰው ነው::

ሙሴ የመሪነት አገልግሎቱን የጀመረው ከእግዚአብሔር አጥርቶ በመስማትና የሰማውን በእምነትና በድፍረት ለፈርዖን በመናገር ነበር:: የመጀመሪያው እርምጃ ከእግዚአብሔር መስማት ነው::

ሁለተኛው የሰማውን ወደ ተላከበት ለፈርዖን ማድረስ ነው። ሦስተኛው ከፈርዖን የሰማውን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነበር።

ሙሴ ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት ከፈርዖን ጋር ንግግር ከጀመረ በኋላ ፈርዖን በእስራኤላውያን ላይ ሥራ አከበደባቸው። የሚሠሩት የጡብ ቁጥር እንዳያንስ ገለባውንም እራሳቸው እንዲሰበስቡ አዘዘ። ፈርዖን በዚህ ድርጊቱ ሕዝብን በማስጨነቅ መግዛት የሚፈልጉ የግፈኛ አስተዳዳሪዎች ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ግን ቀንበርን ይሰብራል።

ሙሴ ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት በጀመረ ጊዜ ፈርዖን በሕዝቡ ላይ ሥራ በማከበዱ ሕዝቡ በሙሴ ላይ ማጉረምረም ጀመረ (ዘጸ 5፡20-21)። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ሙሴ ተመልሶ ወደ ላከው ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

በተዘረጋች እጁ ሕዝቡን ነጻ የሚያወጣ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ፈርዖን ያድኑኛል ያስጥሉኛል ብሎ የተማመነባቸውን በግብጽ የነበሩ አማልክት ሁሉ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል በፈጸመው ታአምራት ቀጣቸው (ዘጸ 12፡12)። በመጨረሻም እርሱ ብቻ አምላክ እንደሆነ በግብጽ ምድር አሳይቶ ሕዝቡን ነጻ አወጣ።

እግዚአብሔር ብቻውን መሥራት ሲቻለው አብረውት እንዲሠሩ ሰዎችን ይጠራል። የእጅ መሣሪያ ሆነው የሚላኩለትን፤ አድርጉ የሚላቸውን የሚፈጽሙትን ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት ምሪትን ከእግዚአብሔር በመቀበል ሕዝብን መምራት ነው። በመሠረቱ ክርስቲያናዊ መሪነት ማለትም ይኸው ነው፤ በእግዚአብሔር መመራት፤ የእርሱ መልእክተኛ በመሆን ፈቃዱን ማገልገል ነው።





## 4. መሪ ፈጽሞ[11] የሚታዘዝና የሚታመን የእግዚአብሔር ባሪያ ነው።

ለምሪት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ አንድ ደረጃ ነው። እግዚአብሔር ለገለጠው ፈቃዱ መታዘዝ ደግሞ ከፍ ያለ ደረጃ ነው። ሙሴ በሕይወት ዘመኑ እግዚአብሔርን የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን እንደተገለጠለት ለማድረግና ለመኖር የተጋ ሰው ነው።

ለምሳሌ የማደሪያውን ድንኳን ለመሥራት እግዚአብሔር «እንዳየው ምስል አድርጎ ይሠራት ዘንድ ሙሴን ተናግሮ እንዳዘዘው...» (ሐዋ 7፡44) ሙሴ ባየው እቅድ መሠረት አስመስሎ በመሥራት ታዘዘ (ዘጸ 26፡30)። «ሙሴና አሮንም ...እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ» (ዘጸ 7፡6)፤ (ሙሴም ...እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ» (ዘጸ 40፡16)።

የሙሴ ታዛዥነት ሥራን ተቀብሎ ለሠራተኞች በማስተላለፍ ብቻ አያበቃም። ከእግዚአብሔር ትእዛዝን ከተቀበለና ሥራውን ለሚሠሩት ካስተላለፈ በኋላ ሠራተኞች በየሙያቸው እንደታዘዙት በትክክል መሥራታቸውን በቅርበት ይመለከታል፤ ይቆጣጠራል። «እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ ሁሉ እንዲሁ የእስራኤል ልጆች ሥራውን ሁሉ ሠሩ። ሙሴም ሥራውን ሁሉ አየ እነሆም አድርገውት ነበር፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘው እንዲሁ አድርገውት ነበር» (ዘጸ 39፡42-43)።

ጌታ እግዚአብሔር ሲናገር «ባሪያዬ ሙሴ ግን ...በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው» (ዘኁ 12፡7) ብሏል። «ባሪያዬ» እና «የታመነ» የሚሉትን ሁለት ቃላት ልብ እንበል። የዕብራውያን ጸሐፊ ሙሴን ከጌታ ኢየሱስ ጋር በማመሳሰል[12] ስለ ታማኝነት ሲጽፍ «ሙሴ ደግሞ

[11] ሙሴ ሰው ነውና ድካም ነበረበት «ፍጹም» አልነበረም። ስለዚህ በዚሁ ምዕራፍ ተራ ቁ.12 የቀረበውን ይመልከቱ።

[12] Antitype-

በቤቱ ሁሉ የታመነ እንደሆነ...» (ዕብ 3:2) እንዲሁም «...በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ» (3:5) ይላል:: የሙሴ መታመን በእግዚአብሔር ሎሌነት (ባሪያነት/ አገልጋይነት) ነው:: ይህም ቤቱ (ማለትም ሕዝቡ) የሆነውን በታማኝነት መምራቱ፤ መጠበቁ፤ ማስማራቱ ነው::

ክርስቲያናዊ መሪ የእግዚአብሔር ባሪያ ነው:: ባሪያ የጌታውን ትዕዛዝ ለማድረግ የተጠራ፤ በጌታው ፈቃድ የሚኖር፤ የተሰጠውንም ኃላፊነት በትክክልና በአግባቡ የሚፈጽም ሰው ነው:: ስለዚህ ለጥሪ ታማኝነት ከመሪዎች ይጠበቃል (ማቴ 25:21፤ ሉቃ 12:42፤ 1ቆሮ 4:2)::

## 5. መሪ ምክርን ለመስማትና አሠራርን ለማስተካከል ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው::

በከፍተኛ የመሪነት ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች አንዱ የሚቸገሩበት ነገር ከሌሎች ሰዎች ምክርን ለመስማት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት ነው:: አንዳንድ ጊዜም እነርሱ ከደረሱበትና ከሚያውቁት በላይ ማንም ሰው አልደረሰም (አይኖርም) ብለው ስለሚያስቡ ማንም ስለ ተሻለ አሠራር ሊመክራቸውና ሊያስተምራቸው እንደሚችል አድርገው አይገምቱም:: ሆኖም በአሠራራቸው ሊስተካከል የሚያስፈልገው ነገር እንዳለ የሚያስቡና ምክርን የሚሰሙ መሪዎች ለመማር የሚፈልጉ[13] ቅን መንፈስ ያላቸው ናቸው::

ሙሴ ከግብጽ ንጉሥ ከፈርዖን ጋር ተከራክሮ ሕዝቡን ነጻ ያወጣ፤ በእጁ ታላላቅ ተአምራት የተደረጉ ታላቅ መሪ ቢሆንም እርሱም ሰው ነውና ብዙ ሊማረው የሚገባ ነገር እንዳለ የተገነዘበ ሰው ነው:: ሙሴ ታላቅ መሪ ቢሆነም ሥራዎችን እንዴት

[13] Teachable spirit





እንደሚያከናውን፤ ሕዝቡን በተሻለ ሁኔታ እንዴት ማስተዳደር እንዳለበት የበለጠ መማር ነበረበት:: ስለሆነም ይዞት የነበረውን የአመራር ዘይቤ ለመፈተሽና አስተዳደራዊ አደረጃጀቱን እንደገና ለማዋቀር አማቱ ዮቶር በመከረው ጊዜ ምክር ሰማ::

የዮቶር ምክር ኃላፊነትንና ሸክምን ስለ ማከፋፈልና ሕዝቡን ስለ ማደራጀት ነበር (ዘጸ 18):: በዘጸ 18:13-26 ከተጠቀሰው በተጨማሪ ሙሴ አደረጃጀቱን[14] በተለያየ ጊዜ አሻሽሏል (ዘኍ 11:16-30 እና ዘዳ 1:13-18ን ይመልከቱ):: ሙሴ ምክር ለመስማት የሚወድ ጥበበኛ ሰው ነው:: ከሌላው ምክርን ለመስማት ትሕትናን ይጠይቃል:: ጥሩ የሚመራ መልካም ምክርን ይሰማል::

## 6. መሪ ኃጢአትንና በእግዚአብሔር አለመታመንን በመቃወም ከአምላኩ ወገን የሚቆም ነው::

እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ተራራ ጠርቶት ለአርባ ቀን ከእርሱ ጋር በነበረበት ጊዜ በእስራኤል መንደር ታላቅ አመጽ እንደ ነበረ በዘጸ 22-23 እናነባለን:: ሕዝቡ ከባርነት ምድር በተዘረጋ እጅ ያወጣቸውን እግዚአብሔርን ረስተው በአሮን መሪነት የወርቅ ጥጃ ሠርተው ይሰግዱ ነበር:: አሮን ወርቁን «ከእጃቸውም ተቀብሎ ...ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤ እርሱም:- እስራኤል ሆይ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አላቸው» (ዘጸ 32:4)::

ሙሴ ከተራራው ሲወርድ ይህን ባየ ጊዜ «የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ወደ እኔ ይምጣ» (ዘጸ 32:26) በማለት ሕዝቡን የእግዚአብሔር ወገን በመሆንና ባለመሆን ለየው:: እግዚአብሔርን

[14] Organizational design.

በመከተል የጸኑት (ሌዋውያን) ወደ ሙሴ ሆኑ፤ ጥጃውን በመከተል በጸኑት ላይ ደግሞ የፍርድ ቃል ተናገረ።

በእስራኤላውያን መካከል የገባው ይህ ኃጢአት ሕዝቡ ነፃ የወጣበትን ዓላማ የሚያጠፋ ነው። ሕዝብን ከአምላኩ የሚያርቅና ዓላማውን ፈጽሞ የሚያዘናጋ ነው። እስራኤልን (ቤተ ክርስቲያንን) የሚያዳክማት ኃጢአት እንጂ መከራ (ጦርነት) አልነበረም (አይደለም)።

የመንፈሳዊ መሪ የውስጥ ጥንካሬው የሚለካው በኃጢአትና በአመፅ ላይ በሚወስደው አቋምና እርምጃ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአት ሲገባና አመጽ ሲበዛ በለሆሳስ የሚመለከት መንፈሳዊ መሪ የእረኝነት ተግባሩን የዘነጋና በተግባሩ ከእግዚአብሔር ወገን ያልቆመ ሰው ነው። ከእግዚአብሔር ወገን የሚቆም መሪ «ቅዱስ በሆነውና ቅዱስ ባልሆነ መካከል፤ በንጹሕና በርኩስ መካከል ያለውን ልዩነት» (ሕዝ 22:26) ያስታውቃል። ከእግዚአብሔር ወገን የሆነ መሪ ሕዝቡን ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር ይጠራል።

የሙሴ የመሪነት ችሎታ የተለካበት አንዱ ሌላ ወቅት የተስፋይቱን ምድር የሰለሉት አለቆች ካመጡት መልስና ከዚያ በኋላ ከነበረው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው። የተመረጡት አሥራ ሁለቱ ሰላዮች የነገድ አለቆች በመሆናቸው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠውን ተስፋ የሚያውቁ፤ ከሙሴ ጋር በቅርብ የሠሩና ሕዝቡ ነጻ ሲያወጣ እግዚአብሔር ያደረገውን ተአምራት የሚያውቁ እንደሚሆኑ ይታመናል። ሁሉም በኢያሱና ካሌብ «ደረጃ» የሆኑ ሰዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል።

አሥራ ሁለቱም ሰላዮች ለሙሴና ለሕዝቡ ያመጡት ሪፖርት ተመሳሳይ ሆኖ እያለ ያዩትን ከተሰጣቸው ተስፋ አንጻር በማገናዘብ ግን ከፍተኛ ልዩነት እንዳለባቸው ግልጽ ሆነ። አሥሩ ወደ ኋላ





መመለስን ሲመርጡ ሁለቱ ወደ ፊት መሄድን መርጠዋል። የሁለቱ ውሳኔ እግዚአብሔር ተናግሯልና ወደ ፊት እንገስግስ ሲሆን የአሥሩ ደግሞ ያየነው የሚያስፈራ በመሆኑ ወደ ግብጽ መመለስ ይሻለናል የሚል ነው። የአሥሩ ሰላዮች ሀሳብ የሕዝቡን ልብ አራደው።

እዚህ ላይ እናስተውል - የሙሴ የአመራር «ፍልስፍና ወይም ስልት» በድምጽ ብልጫ መወሰን ወይም የአብዛኛውን ፍላጎት መፈጸም ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችል ነበር? እንደ ሰው ሲታሰብ «በመሪዎች ጉባዔ» ውስጥ አሥር - ለሁለት (10:2) በሆነ ድምጽ ተወስኖ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጀምሮ የገባው ተስፋ «በከሸፈ» ነበር። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል ሳይሆን መቃወም ነው።

የእግዚአብሔርን ማንነት ያልተረዱና ለሰጠው ተስፋ እምነት የጎደላቸው መሪዎች በአለቅነት ላይ ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ተስፋ ሳይቀር የሚቃወሙ ይሆናሉ። የእግዚአብሔርን አቅምና አሠራር በራሳቸው ችሎታና በሥጋዊ ዓይናቸው በሚያዩት ብቻ የሚወስኑ ይሆናሉ። እንዲህ ዓይነት መሪዎች በሚኖሩበት ዘመን የአብዛኛውን ሕዝብ ድምጽ እስካገኙ ድረስ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመሄድ ይልቅ ወደ ኋላ መመለስን እስከ መምረጥ ይመኛሉ።

ሁለቱ ኢያሱና ካሌብ የተናገሩት ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር በመስማማት በእምነት ስለ መጓዝ ነው። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃልና ያደረገውን ተአምራት የሚረሳ፤ ዛሬ በሚያየው ብቻ የሚታመን ያ ሰው ምስኪን መሪ ነው። እግዚአብሔር ዓላማው ትጸናለችና በሰው ብዛት በተሰለፈውም ሠራዊት ጥንካሬ አይወሰንም።

ሕዝቡ እንደ እግዚአብሔር ቃል በሚኖርበት ዘመን የብዙሃኑ ድምጽ እንደ ቃሉ ይሆናል። አንገቱን ባደነደነበትና ከተጻፈው ቃል

በሰበብ አስባቡ በተቃራኒው በሚሄድበት ወቅት ግን የመሪ ኃላፊነቱ ከባድ ነው:: በዚህ ጊዜ በብዙሃኑ ድምጽ መመራት ከእግዚአብሔር ሀሳብ ተቃራኒ ወደ ሆነ መንገድ ሊወስድ ይችላል:: ይህን የሚለይ «ልዩ መንፈስ» ያለው መሪ ያስፈልጋል::

እንዲህ ባለ ዘመን ለጊዜውም ቢሆን ራስን በመሪነት ቦታ (በወንበር ላይ) ለማቆየት አንዱ መንገድ ሕዝቡ የሚፈልገውን ማድረግ ነው:: ይህ አሠራር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው:: በድንጋይ መወገር (ከወንበር መውረድም) ቢሆን (ዘኁ 14:4) እንደ ቃሉ ለሆነው ነገር በድምጽ ብዛት ሳይመራ የእግዚአብሔርን ሀሳብ መከተል አለበት:: በእግዚአብሔር የተመረጠ መሪ የጠሪውን ሀሳብ የሚያገለግል ነው::

## 7. መሪ በእርሱ ላይ ከሕዝቡ የሚነሣን ማጉረምረምና ተቃውሞ በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል ነው::

አብዛኛውን ጊዜ ሕዝብ ለምን ያጉረመርማል? አንድም የአስተዳደር በደል ደርሶበት፤ ወይም በውሸት በሚያነሳሱት ሰዎች ተታልሎ፤ ያለዚያም በእግዚአብሔር ላይ እምነት አጥቶ ሊሆን ይችላል:: የማጉረምረሙ መነሻ አድልዎ ወይም የአስተዳደር በደል ቢሆን ፈጥኖ አሠራሩን መገምገምና ማስተካከል ይገባል:: መነሻው በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት በመጣል በምኞቱ በመወሰድ ከሆነ መፍትሔው «ይበልጥ መንፈሳዊ» ይሆናል::

ሙሴ በእግዚአብሔር ላይ የሚያጉረመርምን ሕዝብ ይመራ ነበር:: አንዱ መገለጫው ራሱ ሙሴን መቃወምና ለመውገርም እንኳ መነሳሳት ነበር:: በሙሴ ላይ የተነሣው ተቃውሞና ማጉረምረም ብዙ መልክ ያለው ነበር:: ጥቂቶቹን እንመልከት::

- ሽታችንን አግምታችሁታልና የሚል ተቃውሞ (ዘጸ 5:21)





- በራብ ልትገድሉን እኛን አውጥታችኋል (ዘጸ 16:1-4):: ይህን ያሉት ከግብጽ ከወጡ ገና በ6ኛ ሳምንታቸው አካባቢ ነው::
- የምንጠጣውን ውኃ ስጠን ብለው ተጣሉት (ዘጸ 17:1-2)
- ወንድሙ አሮንና እህቱ ማርያም «ቀኑበት» (ዘኁ 12)
- በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸን ብንገዛላቸው ይሻለናል ተወን ብለንህ ነበር አሉት (ዘጸ 14:11-12)
- ሕዝቡ ድምጻቸውን አንስተው ጮሁ አለቀሱ (ዘኁ 14:1-4)
- በድንጋይ ለመውገርም አሰቡ (ዘኁ 14:10)
- አብረውት የሚያገለግሉት እነ ዳታንና ቆሬ በእርሱ ላይ ክፉ ተናገሩ (ዘኁ 16)
- ሌላ መሪ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ አሉ (ዘኁ 14:4)

ይህ ሁሉ መነሳሳትና ተቃውሞ በሙሴ ላይ ደረሰ:: «ሙቀቱን መቋቋም ካልቻልክ ወደ ምድጃ አትቅረብ» እንደሚባለው አንድ ሰው ወደ መሪነት ቦታ ሲመጣ ተቃውሞና የሕዝብ ማጉረምረም ሊኖር እንደሚችል አስቦ መግባት አለበት::

ሙሴ ተቃውሞን የማስተናገድ ታላቅ ጥበብ ነበረው:: ጥበቡም በትሕትና መመላለሱና አዘውትሮ ወደ እግዚአብሔር መቅረቡ (መጮኹ) ነው:: ሥራው የእግዚአብሔር እንደሆነ ጠንቅቆ ስለተረዳና «የራሱ የግል አጀንዳ» ስላልነበረው ጉዳዩን «ለዋናው መሪ ለእግዚአብሔር» በማቅረብ (ይግባኝ በማለት) ለሁኔታው የሚስማማ ምሪትንና ብይንን ከታላቁ መሪ ከሠራዊቱ አለቃ ይቀበል ነበር:: ሙሴ በሕዝቡ ማጉረምረም ተስፋ ያልቆረጠ፤ መሪነቱንም ያልተወ፤ በተጠራበት አገልግሎት የዘለቀ መሪ ነው::

## 8. መሪ የሚመራውን ሕዝብ የሚወድ፤ ስለ ሕዝቡ የሚጸልይና የሚማልድ ነው::

መሪ የራሱን የሚፈልግ ሳይሆን ለሌላው ፍቅር ያለው በጎውን የሚያስብ መልካም እረኛ ነው:: በሕዝብ ላይ የሚደርሰው ችግር «እኔን እስካልነካኝና እስካልኮሰኮሰኝ ድረስ ስለሌላው እግዚአብሔር ያውቃል» በሚል ዓይነት አስመሳይ መንፈሳዊነት የሚሄድም አይደለም:: መጽሐፍ «ዋኖቻችሁ ...ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ» (ዕብ 13:17) እንደሚል አንድ ሰው ወደ መሪነት ሲመጣ እርሱ ስለሚመራቸው ሰዎች ሕይወት የመጠንቀቅና የመጸለይ ኃላፊነት አለበት:: ይህ መልካም እረኝነት ነው::

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተቆጥቶ ሕዝቡን ሊያጠፋው ለሙሴ «...በቸነፈር እመታቸዋለሁ አንተንም ከእነርሱ ለሚበዛና ለሚጠነክር ሕዝብ አደርግሃለሁ» (ዘኁ 14:12) ሲለው የሙሴ መልስ «...እባክህ እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል» (14:19) የሚል የምልጃ ጸሎት ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ «ታላቅና ብዙ» ነገር ለመሪ ደስ የሚል ቢሆንም የሙሴ ትኩረት የእግዚአብሔር ዝና በመውጣቱና ስሙ በመከበሩ ላይ ነበር (14:16-18)::

በሌላም ሁኔታ «ወዮ እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል ...ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ» (ዘጸ 32:31-32):: ሕዝቡን የሚወድ መሪ ለራሱ ከሚሆንለት መልካም ነገር ይበልጥ ስለሚመራው ሕዝብ ያስባል:: ሙሴ በመሪነቱ ወደ መጨረሻ ዓመታት ስለሄደበት ጉዞ ሲያስታውስ «እግዚአብሔርም:- አጠፋችኋለሁ ብሎ ስለ ተናገረ በወደቅሁበት ዘመን አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በእግዚአብሔር ፊት ወደቅሁ:: ...ጸለይሁ ...ሕዝብህንና ርስትህን አታጥፋ...» (ዘዳ 9:25-29) ብሎ እንደ ማለደ ይገልጻል:: የሚማልድ መሪ ባለበት





የእግዚአብሔር ቁጣ ይመለሳል (ዘኁ 11:1-3)፤ መቅሰፍት ይከለከላል (ዘኁ 16 )::

ዘማሪው «...ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ...» (መዝ 106:23) እንዳለው የሕዝብ እረኛ የሆነ መሪ በሕዝብ ላይ የሚመጣ መቅሠፍት እንዲከለከል በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሕዝቡ የሚቆም፤ ሕዝቡን የሚወድና የሚጸልይ በደልም ሲኖር ከእግዚአብሔር ምሕረት የሚማልድ ነው:: ይህም ሳሙኤል «...ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ» (1ሳሙ 12:23) እንዳለው ነው::

## 9. መሪ በእግዚአብሔር ፊት ትሑት የሆነ ሰው ነው::

የሙሴ ወንድም አሮንና እህቱ ማርያም በሙሴ ላይ መናገር በጀመሩ ጊዜ ጌታ እግዚአብሔር «ባሪያዬ ሙሴ ...በቤቴ ሁሉ የታመነ» የሚለው «በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ» (ዘኁ 12:3)::

ትሑት:- በራሱ የማይታመን፤ ከአምላኩ በቀር በሌላ የማይደገፍ፤ ለመማር የሚወድ፤ ምክር የሚሰማ ሰው ነው:: ትሑት ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የሚቆርጥ፤ እርሱን ደስ ለማሰኘት የሚወስን ሰው ነው:: እንዲህ ዓይነት ሰው በሰዎች ዘንድ ድጋፍ የማያስገኝለትን ውሳኔ እንኳን መወሰን ካለበት ከእግዚአብሔር ወገን ይቆማል:: ሙሴም ይህን አድርጎአል (ዘጸ 32:26)::

ትሑት የሆነ ሰው:- መከናወንን ባገኘ፤ እውቀትና ሀብት በበዛለት ጊዜ ያለውን በእኔ ጉልበትና ጥረት አገኘሁት የማይል ሰው ነው:: ሙሴ ሕዝቡንም ሲያስተምር «...አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ፤ በልብህም:- ጉልበቴ የእጄም ብርታት ይህን ሀብት

አመጣልኝ እንዳትል:: ...ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ» (ዘዳ 8:17-18) አለ:: ትሑት ሰው ያገኘው መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተሰጠው በማወቅ (ያዕ 1:17) እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ነው::

ትሑት የሚመስል ሰው በእርግጥም ትሑት እንደሆነ የሚለየው ምኞቱን ሲያገኝ፣ ሲበረታ ወይም የፈለገውን «ከፍተኛ» የአገልግሎት ደረጃ ደርሶ በትሕትናው የዘለቀ እንደሆነ ነው:: ሰዎች በመሪነት ወይም በክብር ቦታ ለጥቂት ዓመታት ከቆዩ በኋላ ሲቀየሩ ወይም እውነተኛው ማንነታቸው ሲገለጥ ማየት አዲስ ነገር አይደለም::

በመጽሐፍ ቅዱስ ሳዖልና ዖዝያን ለዚህ ምሳሌ ይሆኑናል:: ሳሙኤል ሳዖልን ለንጉሥነት ሊቀባው ሲፈልገው ታናሽነቱን ያወቀና የተደበቀ ሰው ነበር:: ከጥቂት የንጉሥነት ዓመታት በኋላ ሳዖል ያን «ትሕትናው» ጥሎ በእግዚአብሔር ላይ የታበየ ለመታዘዝ ያልፈለገ ንጉሥ ሆነ (1ሳሙ 15:27):: እንዲሁም ዖዝያን እግዚአብሔርን በመፈለግ የጀመረ እርሱንም ይፈራ የነበረ ንጉሥ ነበር:: «ነገር ግን በበረታ ጊዜ ለጥፋት ልቡ ታበየ አምላኩንም እግዚአብሔርን በደለ» (2ዜና 26:16)፤ ካህናቱም ሲመክሩት ተቆጣቸው (26:17-18)::

እንግዲህ በመሪነት የእግዚአብሔር ባሪያ ሆኖ መዝለቅ ይጠበቃል:: በትሕትና ጀምሮ በትሕትና መጨረስ እግዚአብሔርን አለመበደል ነው:: ትሑቱ ሙሴ በዕድሜው መጨረሻም አካባቢ እስራኤላውያንን የሚመክራቸው በቀደመው ዘመን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን እንዳይረሱ ነው:: ትሕትና እዚህ የደረስኩት በእግዚአብሔር ነው፤ አሁንም አቅሜ፣ ጉልበቴ፣ ኃይሌ፣ መከናወኔ እርሱ ነው ማለት ነው::





## 10. መሪ ለችግር ጊዜያዊ መፍትሔ ከመፈለግ በተጨማሪ በችግሩ ምንጭ ላይ በማትኮር ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥ ነው::

ሙሴ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ወደ ተራራው ሲወጣ ኃላፊነቱን ለአሮንና ሖር ሰጥቶ ነበር:: እንደወከላቸውም ለሕዝቡ ሲገልጽ «ሽማግሌዎችንም:- ወደ እናንተ እስክንመለስ ድረስ በዚህ ቆዩን አሮንና ሖርም እነሆ ከእናንተ ጋር ናቸው:: ነገረተኛም ቢኖር ወደ እነርሱ ይምጣ» (ዘጸ 24:14) በማለት ገልጾአል:: ይህ ሁሉ ሆኖ ሙሴም የት እንደሄደ እየታወቀ እስራኤላውያን አሮንን «ይህ ከግብጽ ምድር ያወጣን ሰው ምን እንደሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት» (ዘጸ 32:1):: ከዚህ የተነሣ በእስራኤል ሰፈር ትልቅ ችግር መጣ::

ሕዝቡ ችግራችን ነው ያሉትን ተናግረው ራሳቸው የመፍትሔ ሀሳብ ሰጡ:: ችግሩ ‹መሪ የለንም› ሲሆን መፍትሔው ‹የሚመሩን አማልክት እንፈልጋለንና አሮን አማልክቱን ይቅረጽልን› የሚል ነው:: ለዚህ የሕዝብ ጥያቄ (ፍላጎት) ካህን የሆነውና ሙሴ የወከለው አሮን የሰጠው መልስ በሃሳቡ በመስማማት ወርቅ እንዲሰበሰብና የወርቅ ጥጃ እንዲሠራ ነው:: ይገርማል!!

ሙሴ ከተራራ ሲመለስ በእስራኤላውያን ሰፈር የነበረውን ጩኸት ሰምቶ ችግር እንዳለ ባወቀ ጊዜ ችግሩ ለምን እንደመጣ ይረዳል:: ሙሴም አሮንን:- ይህን ታላቅ ኃጢአት ታመጣበት ዘንድ ይህ ሕዝብ ምን አደረገህ? (ዘጸ 32:21) አለው:: ችግሩ «ታላቅ ኃጢአት» እንደሆነ ምንጩን ይገነዘባል::

የአሮን አመራር ‹የሕዝቡን ፍላጎት (ጥያቄ) እንዴት ላሟላ? ሕዝቡን እንዴት ደስ ላሰኘው?› የሚል ነው:: የሙሴ አመራር ‹ይህ ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ይታያል?› የሚል ነው::

ታላላቅ መሪዎች ከመለስተኞች የሚለዩት ለአንድ ችግር መፍትሔ ከመፈልግ በተጨማሪ በችግሩ ምንጭ ላይ በማትኮር መሠረታዊ ማስተካከያ በማድረግ ችሎታቸው ላይ ነው። ይህ ትልቅ የአመራር ጥበብ ነው።

### 11. መሪ አስተዳደሩን የሚያደራጅ፣ ተተኪ-መሪን የሚያዘጋጅና ቀጣዩን ትውልድ የሚያስተምር ነው።

በሙሴ መሪነት ሥር የወገን አለቆች ነበሩ፣ ሰባዎቹንም ሾማአል (ዘኍ 11:16-17)። ሕዝቡን ለማስተዳደርና ፍርድ ለመስጠት በየደረጃው የተሾሙና ሥራውን በኃላፊነት የሚመሩ ሌሎችም ብዙዎች ነበሩ። እንዲሁም ከእርሱ ጋር በቅርበት የሚሠራና የሚረዳው ሎሌ (አገልጋይ) የሆነው ኢያሱ ነበር (ዘጸ 24:13፣ 33:11፣ ዘኍ11:28፣ ኢያ 1:1)።

ከዮቶር ምክር በመነሳት ሙሴ ሕዝቡን ያደራጀው የሺህ አለቆች፣ የመቶ አለቆች፣ የአምሳ አለቆች፣ የአሥር አለቆች በመሾም ነው (ዘጸ 18:21)። ለአንድ ሺህ ሕዝብ አንድ መሪ፣ አሥር ባለ መቶ አለቃ መሪ፣ ሃያ ባለ ሃምሳ አለቃ መሪና መቶ ባለ አሥር አለቃ መሪዎችን እንደ ማለት ነው። ስለዚህ በአንድ ሺህ ሕዝብ መካከል አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ያህል በተለያየ ደረጃ የተቀመጡ መሪዎች ነበሩ ማለት ነው። ጠቅላላ የነበረው ሕዝብ (እግረኛው) ስድስት መቶ ሺህ ነበርና (ዘጸ 12:37) በተለያየ ደረጃ የነበረው የመሪዎች ቁጥር 78600 ያህል ነበር። ይህን መሰል ሰፊ መዋቅራዊ አደረጃጀት መገንባትና መምራት ትልቅ ችሎታን ይጠይቃል።

በአንድ ድርጅት ውስጥ ሁሉንም ተግባር በጥሩ ሁኔታ ማከናወን ብቻውን እንደማይችል ያስተዋለ መሪ ሥራዎችን ከፍሎና ከፋፍሎ ለሌሎች ይሰጣል። ይህን በማድረጉ ሌሎች ብዙ ሰዎች ሥራ እንዲለማመዱ መሪዎችም እንዲያድጉ ያደርጋል። መሪው ይህን





በማድረጉ ለራሱ በቂ ጊዜ እንዲያገኝና በጥቂትና ዋና ተግባሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ጥራት ያለው ሥራ እንዲያከናውን ይረዳዋል። ስለዚህ የአሠራር ቅልጥፍናን በሚመለከት ከዮቶር ምክር ብዙ ትምህርት ይገኛል (ዘጸ 18)።

እንዲሁም ሙሴ ከእርሱ ዘመን በኋላ ስለሚመጣው ትውልድ አስተዳደግ ያሰበ መሪ ነው። በዘዳ 28:1-19 ባለው እንደምንመለከተው ምድረ በዳ የተወለዱት ልጆች እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጠውን የተስፋ ምድር ይወርሱ ዘንድ እንዴት መኖር እንዳለባቸውና ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ይመክራቸዋል። የምክሩ ዋና መልእክት እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ፣ በእርሱ እንዲታመኑና ሕጉን እንዲጠብቁ ነው። በተጨማሪም በረከት እንዴት እንደሚያገኙና እርግማን ደግሞ እንዴት ሊመጣባቸው እንደሚችል በዝርዝር ይነግራቸዋል። ስለሆነም ሙሴ እንደ አባት ቀጣዩን ትውልድ መክሯል፣ አስተምሯል።

ተተኪ መሪን በማዘጋጀት የሙሴ ምሳሌነት ትልቅ ነው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ወደ ተራራ ሲሄድ ኢያሱ አብሮት አቅንቶ በተፈቀደው ቅርበት ሆኖ ይቆያል፣ በሙሴ መሪነት በጦርነት ተሰልፎአል። ኢያሱ የማደሪያውን ድንኳን ይጠብቅ ነበር። የማደሪያውን ድንኳን አይተውም ነበር (ዘጸ 33:7-11)። እንዲህ በማድረግ ሥራን ማስለመድና ኃላፊነትን በማካፈል ማለማመድ ተተኪን የማዘጋጀት ተግባር ክፍል ነው።

ይሁን እንጂ ኢያሱን ለመሪነት ያዘጋጀው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑንም ልብ ማለት ይጠቅማል። ኢያሱን ለማዘጋጀት ሙሴ ሊያደርገው የሚገባውን እግዚአብሔር ይነግረው ነበር። ለምሳሌ እስራኤል አማሌቅን ከመታ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን «…ይህን ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፈው በኢያሱም ጆሮ ተናገር አለው» (ዘጸ

17:14):: እንዲሁም «እግዚአብሔርም ሙሴን አለው:- መንፈስ ያለበትን ሰው የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን ጫንበት፤ ...እግዚአብሔርም በሙሴ እንደ ተናገረ እጁን በላዩ ጫነበት፤ አዘዘውም» (ዘኍ 27:18-23):: በመጨረሻም እግዚአብሔር «የነዌንም ልጅ ኢያሱን:- የእስራኤልን ልጆች ወደ ማልሁላቸው ምድር ታገባለህና ጽና አይዞህ፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ ብሎ አዘዘው» (ዘዳ 31:23)::

ከሙሴ ለሰባዎቹ ሽማግሌዎች መንፈስ በወሰደበት ጊዜ የሙሴን ክብር ወይም ሥልጣን እንዳልቀነሰበት ሁሉ (ዘኍ 11:17) በመንፈሳዊ መሪነት ሌሎችን በአገልግሎት ማሳደግና ኃላፊነትን ማካፈል በመሪው ላይ ያለውን ጸጋ አይቀንስበትም:: ቀድሞ የበራ ሻማ ሌላውን ሲለኩስ የለኳሹ ሻማ ብርሃን ወይም ኃይል እንደማይቀንስ በመንፈሳዊውም ዓለም ብዙዎች በአገልግሎት እንዲሰማሩ ማድረግ የአስተማሪውን (የመሪውን) ጸጋ አይቀንስበትም::

12. ሙሴም «እንደ እኛ ሰው ነበረ»

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ተከራከረ::

ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ነፃ እንዲያወጣ በተጠራ ጊዜ በተደጋጋሚ ለእግዚአብሔር የሰጠው መልስ የሚከተለው ነበር::

የመጀመሪያው:- «እኔ ማነኝ?» (ዘጸ 3:11):-

ሙሴ ከአርባ ዓመታት በፊት መሪ እንደሚሆን መስሎት ነበር:: ከምድያም መልስ ግን ለቦታው አለሙብቃቱን አይቶአል:: እግዚአብሔርም «እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ» (3:12) አለው:: የክርስቲያናዊ መሪነት አቅም ከተጠራው ሰው እውቀት፤ ልምድ፤ ብርታትና ችሎታ ሳይሆን ከጠሪው ማንነት የተነሣ የሚገኝ ነው::





ሁለተኛው:- «ስሙስ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ?» (3:13)::

የላከው «ያለና የሚኖር:- እኔ ነኝ» (3:14) አለው:: ሁለት ሚሊዮን ያህል ሕዝብ ለመምራት የሚልከው ማንነትና ሥልጣን መታወቅ አለበት:: ይህ ላኪ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ጉዞ የመንገድ ፍላጎት የሚያሟላ መሆን አለበትና::

ሦስተኛው:- «አያምኑኝም ቃሌንም አይሰሙም:- እግዚአብሔርም ከቶ አልተገለጠልህም ይሉኛል» (4:1)::

ይህ አባባል ቀደም ሲል «በእኛ ላይ አንተን አለቃ ወይስ ዳኛ ማን አደረገህ?» (2:14) ያሉትን ያሳስባል:: ሙሴ አሁንም ሕዝቡ ላይቀበሉት እንደሚችሉ ገምቷል:: እግዚአብሔር የሚሰጠው መልስ እነርሱን የሚያሳምን ምልክቶች እንደሚያደርግ ነው (4:4-9):: ከዚህ በኋላ ሙሴ ወደ ዋናው ጥያቄ (ክርክር) ይመጣል::

አራተኛው:- «ጌታ ሆይ፤ እኔ አፈ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ» (4:10)

ሙሴ: ኮልታፋ መሆኑን ለፈጣሪው ይነግረዋል:: የእግዚአብሔር መልስ ግን ኮልታፋነቱን እንደሚያውቅና የፈጠረውም እርሱ መሆኑን እንዲሁም ቢታዘዝ ከአፈ ትብ ጋር መሥራት የሚችለውን ያህል ከኮልታፋም ጋር መሥራት እንደሚችል ይነግረዋል (4:11-12):: ቁም ነገሩ የሰውየው ችሎታ ወይም ማንነት (ወይም ካሪዝማ) ሳይሆን እግዚአብሔር ከዚያ ሰው ጋር መሆኑ እንደሆነ ያስረዳዋል::

አምስተኛው:- «በምትልከው ሰው እጅ ትልክ ዘንድ እለምንሃለሁ»[15] (4:13)

ሙሴ ይህን በማለቱ የእግዚአብሔር ቍጣ በሙሴ ላይ ነደደ:: አሮንም እንዲረዳው አደረገ:: «አንተም ትናገረዋለህ ቃሉንም በአፉ

[15] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «እባክህ ሌላ ሰው ላክ»

ታደርገዋለህ፤ እኔ ከአፍህና ከአፉ ጋር እሆናለሁ፥ የምታደርጉትንም አስተምራችኋለሁ» (4፡15) አለ።

ይህ ሁሉ ጥያቄና ክርክር ሙሴ «እንደ እኛ ሰው» እንደነበረ ያስገነዝበናል:: የእግዚአብሔርን ማንነትና ድንቅ አሠራር በሙላት አልተረዳም ነበር:: እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ‹አባብሎ› ወደ መሪነት አደረሰው::

ለ. እግዚአብሔር ሊገድለው የፈለገ ሰው ነው::

በብሉይ ኪዳን ወንድ ልጁን የማይገርዝ ቤተሰብ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ቃል ኪዳን የናቀ በራሱም ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚጋብዝ ነው:: እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ እንዲያወጣ የተጠራ ሙሴ ይህን ቃል ኪዳን በመጠበቅ ልጁን ባለመግረዙ «እግዚአብሔር ተገናኘው ሊገድለውም ፈለገ...» (ዘጸ 4:24):: ግን «ሲፓራም ሚስቱ ባልጩት ወሰደች፣ የልጅዋንም ሸለፈት ገረዘች» (4:25):: ይህች አስተዋይና ፈጣን ሴት ሊሆን የሚገባውን ፈጥና በማድረግ ሙሴ እንዳይሞት ምክንያት ሆነች::

ሐ. የእግዚአብሔርን ክንድ ታላቅነት በሙላት ያልተረዳበት ጊዜ ነበር::

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በምድረ በዳ ለወር ሙሉ ሥጋ እሰጣችኋለሁ ሲል «ሙሴም እኔም በመካከላቸው ያለሁ ሕዝብ ስድስት መቶ ሺህ እግረኛ ናቸው:: አንተም፡- ወር ሙሉ የሚበሉትን ሥጋ እኔ እሰጣቸዋለሁ አልህ:: እነርሱን የሚያጠግብ የበሬና የበግ መንጋ ይታረድን? ወይስ የባሕር ዓሣ ሁሉ ያጠግባቸው ዘንድ ይሰበሰብላቸዋልን?» (ዘኁ 11:21-22) በማለት የእግዚአብሔርን ችሎታ ጠየቀ:: «እግዚአብሔርም ሙሴን፡- በውኑ የእግዚአብሔር እጅ አጭር ሆነ? አሁን ቃሌ ይፈጸም ወይም አይፈጸም እንደ ሆነ አንተ ታያለህ አለው» (11:23)::





እስቲ የሙሴን ችግር ለማየት እንሞክር:: ለ600,000 እግረኛ (ወይም ለ2,000,000 ያህል ሕዝብ) ለወር ስንት በግ ይበቃል? በአነስተኛ ስሌት አንድ በግ በቀን ለአሥር ሰው ቢሆን ለወር የሚያስፈልገው የበግ ብዛት 6,000,000 መሆኑ ነው:: እንግዲያውስ ይህን ያህል በግ በሲና ምድረ በዳ ከየት ይመጣል? ሙሴስ ምን ያድርግ ያስብላል እኮ!! ግን ታላቁ የሕዝብ መሪ ያልተገነዘበው ነገር ሥጋን ለሕዝቡ ለመስጠት እግዚአብሔር ነፋስንም እንኳ እንደሚያዝ ነበር (11:31)::

መ. ከድንጋይ ውኃ እንዲፈልቅ የታዘዘውን በእምነት አላደረገም::

ሙሴ ከድንጋይ ውኃ እንዲፈልቅ እንደታዘዘው ባለማድረጉ የተስፋይቱን ምድር በርቀት ያየ ነገር ግን ወደ እርሷ እንዲገባ ያልተፈቀደለት ሰው ሆነ:: እግዚአብሔርም ሙሴን፡- «በትርህን ውሰድ አንተና ወንድምህ አሮን ማኅበሩን ሰብስቡ ድንጋዩም ውኃን እንዲሰጥ እነርሱ ሲያዩ ተናገሩት ከድንጋዩም ውኃ ታወጣላቸዋለህ» (ዘኁ 20:7-8) አለው:: «እንደታዘዘ በትሩን ከእግዚአብሔር ፊት ወሰደ» (20:9)፤ ነገር ግን «ሙሴና አሮንም፡- ጉባኤውን በድንጋዩ ፊት ሰብስበው፡- እናንተ ዓመፀኞች እንግዲህ ስሙ፤ በውኑ ከዚህ ድንጋይ ውኃን እናወጣላችኋለን? አላቸው::» ከሁለቱ ትዕዛዝ አንዱን ብቻ በትክክል አደረገ::

ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ሙሴን «ዓለቱንም ትመታለህ፤ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል አለው:: ሙሴም ...እንዲሁ አደረገ» (ዘጸ 17:6) ተብሎ ተጽፎአል:: በእግዚአብሔር ትእዛዝ ድንጋይን በመምታት ውኃ ወጥቶ ነበር:: አሁን ደግሞ የታዘዘው ለድንጋዩ እንዲናገር ነው (20:8)፤ ሙሴ ግን «ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው» (20:11):: መምታት ብቻ ሳይሆን ለምን ይሆን የደገመው? የእግዚአብሔርን ውኃ የማፍለቅ ችሎታ (ሥልጣን) ባይጠራጠርም ልክ እንደታዘዘው ግን አላደረገም::

ሙሴ እንደታዘዘው ለድንጋዩ ከመናገር ይልቅ ለሕዝቡ በቁጣ ተናገረ፡፡ ስለሆነም «እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን፡- በእስራኤል ልጆች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁምና…» (20:12) አለ፡፡ በሌላም ቦታ «ሙሴ ተበሳጨ፤ በከንፈሮቹም በስንፍና ተናገረ» (መዝ 106:33) ተብሎአል፡፡ በሕዝቡ ፊት ሁሉን የሚችለውን እግዚአብሔርን ስለ ሰጭነቱ በአክብሮት አልተናገረም፡፡

ሙሴ በአጠቃላይ የሚታወቀው እንደተገለጠለት አስመስሎ በመሥራት ሲሆን እዚህ ላይ ሙሴ ምን ሆነ? ይህ ድርጊት የሆነው እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ ከ38 ዓመት[16] ያህል በኋላ በመሆኑ በሕዝቡ የመሰላቸት (የመማረር) ሁኔታ እንደሚኖር ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጂ ሕዝቡ እንኳን አስቸጋሪ ሲሆን መፍትሔው ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋንና ጥበብን መለመን (ያዕ 1:5) እንጂ መሪ በሕዝቡ ሁኔታ መበሳጨት የለበትም፡፡ ከበረከት ያጎድላል፡፡

ውኃ ወጥቶአል፤ ሕዝቡም ጠጥቶአል፤ ውኃው የተገኘበት መንገድ ግን እግዚአብሔርን የሚያከብር አልነበረም፡፡ ስለዚህ በአንድ አገልግሎት ውጤት መገኘቱ በራሱ በቂ አይደለም፤ በዚያ

[16] "After thirty-eight years' tedious abode in the wilderness, the armies of Israel advanced towards Canaan again. There was no water for the congregation.... But Moses and Aaron acted wrong. They took much of the glory of this work of wonder to themselves; "Must we fetch water?" As if it were done by some power or worthiness of their own. They were to speak to the rock, but they smote it. Therefore it is charged upon them, that they did not sanctify God, that is, they did not give to him alone that glory of this miracle which was due unto his name. And being provoked by the people, Moses spake unadvisedly with his lips." MHCC.





አገልግሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸሙና እርሱ መከበሩ፤ ስሙ መቀደሱ ጭምር እንጂ፡፡

በማጠቃለል፡- ሙሴ፡- በግብፅ ምድር በባርነትና በመከራ ውስጥ የነበሩ የእስራኤል አስራ ሁለት ነገዶችን አንድ አድርጎ የመራ ብርቱና ጽኑ ሰው ነው፡፡ ሙሴ በባርነት ከኖረና በሥራ እጅግ ከደከመ ሕዝብ እግዚአብሔርን የሚያመልክና የበረታ ሠራዊት ያዘጋጀ ታላቅ መሪ ነው፡፡ ሙሴ ሕግንና ሥርዓትን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ የአምልኮ ሥርዓት ያደራጀና ሕዝቡን በመልካም ያስተዳደረ ትሑት መሪ ነው፡፡

የሙሴ የመሪነት መታወቂያ የእግዚአብሔር ሰው (1ዜና 23:14፤ 2ዜና 30:16)፤ የእግዚአብሔር ባሪያ (ዘዳ 33:1፤5፤ ኢያ 1:13፤15፤ 9:24፤ 14:7፤22:5፤ 1ነገ 8:53፤ 2ነገ 18፤12፤ 1ዜና 6:49፤ 2ዜና 1:3፤ 2ዜና 24:9፤ ነህ 10:29፤ ዳን 9:11፤ ራእ 15:3) የሚል ነው፡፡ ሙሴ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የነበረ ሰው (ኢያ 1:5) ነው፡፡ አዎ! የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመራ ታማኝ የእግዚአብሔር ባሪያ ነበር፡፡